አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን

ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሁፍ ፎክሎር ትምህርት ክፍል


# የአንብቦ መረዳት ክሂል ፍተሻ፤ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ማሳያነት


በ

ወርቅነህ ይርጋ ደምሴ



ነሀሴ፣ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የአንብቦ መረዳት ክሂል ፍተሻ፤ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ማሳያነት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሁፍ ፎክሎር ትምህርት ክፍል

አማርኛን በማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

ወርቅነህ ይርጋ ደምሴ

የጥናቱ አማካሪ፤ ግርማ ገብሬ (ዶ/ር)

ነሐሴ፣ 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሁፍ ፎክልር ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ይህ "በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ፍተሻ" በሚል ርዕስ በወርቅነህ ይርጋ የተዘጋጀው ጥናት በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያነት ቀርቦ በውጭና በውስጥ ፈታኞች ተገምግሞ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

የፈተና ቦርድ አባላት

1. አማካሪ ---------------------------- ፊርማ ------------ ቀን ----------------

2. የውጭ ፈታኝ ----------------------- ፊርማ ----------- ቀን -------------

3. የውስጥ ፈታኝ ----------------------- ፊርማ ----------- ቀን -------------

# አህጽሮተ ጽሁፍ

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ደረጃን መመርመር ነው። የጥናቱ ንድፍ ከመጠናዊ ምርምር የሚመደብ ሲሆን ገላጭ የምርምር ስልትን ተከትሎ ተካሂዷል። ጥናቱ ፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት በአመቺ ንሞና ዘዴ፣ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በዓላማ ተኮር የንሞና ንሞና ዘዴ እንዲሁም ተጠኚ ሶስት መማሪያ ክፍሎችን በእጣ (በሎተሪ) ንሞና ዘዴ በመምረጥ ተማሪዎችን በመረጃ ምንጭነት አካቷል። አጥኚው የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት የአንብቦ መረዳት ፈተና፣ የንባብ ትምህርት አተገባበርን ለመፈተሸ የክፍል ውስጥ ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ ተጠቅሟል። በጥናቱ ውጤት መሰረትም በጥናቱ የተሳተፉ 194 ተማሪዎች በመጀመሪያው ፈተና (የሚጠበቅ ውጤት 18.75፣ የተመዘገበ አማካይ ውጤት 14.19)፣ በሁለተኛዉ ፈተና (የሚጠበቅ ውጤት 18.75፣ የተመዘገበ አማካይ ውጤት 14.71) በአጠቃላይ ፈተና ውጤት ደግሞ (የሚጠበቅ ውጤት 37.50፣ የተመዘገበ አማካይ ውጤት 28.90) ሆኖ ተመዝግቧል። ይህም የተመዘገበው በአማርኛ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤት* ከሚጠበቀው ውጤት እንደሚያንስ (ዝቅተኛ መሆኑን) *ያመለክታል። በጥናቱ የተሳተፉ 99 ወንድ እና 95 ሴት በድምሩ 194 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አማካይ ውጤት በአጠቃላይ አንብቦ መረዳት ፈተና ወንድ ተማሪዎች 30.0606 እና ሴት ተማሪዎች 27.6947 ሆኖ ተመዝግቧል። በተመሳሳይ የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Sample t-test) ስታትስቲክስ ውጤት ማየት እንደሚቻለዉ ተጠኚ ተማሪዎች ባስመዘገቡት አጠቃላይ በአማርኛ አንብቦ የመረዳት አማካኝ ውጤትና በሚጠበቀው ውጤት መካከል ያለዉ የልዩነት ጉልህነት ደረጃ የወንድ ተማሪዎች t(98) = 2.393 P<0.018 እንዲሁም የሴት ተማሪዎች t(94) = 2.405 P<0.017 ሆኖ ስለተገኘ ከመቁረጫ ነጥብ (0.05) አንሷል። ይህም በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በወንዶችም በሴቶችም ተማሪዎች የተመዘገበው አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው ውጤት በታች (ዝቅ ብሎ) ሆኖ መገኘትና ከሴቶች ይልቅ ወንዶች የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸዉ በስታስቲክስ ጉልህ (ተቀባይነት ያለዉ) መሆኑን ያመለክታል። በምልከታ በተገኘዉ ዉጤት መሰረት ተጠኚ መምህራን በቅድመ ንባብ እና በንባብ ጊዜ ተግባራት ላይ ጥቂት ድክመቶች (ወጣገባነት) የተስተዋለባቸው ቢሆንም እንደ አጠቃላይ ሲታይ ጠንካራ (የተሻለ) መሆናቸዉ ተረጋግጧል። በተቃራኒው በድህረ ንባብ ትምህርት ተግባራት ደረጃ በጣም ደካማ መሆናቸው ተረጋግጧል። በመጨረሻም አጥኚው የጥናቱን ግኝት መሰረት በማድረግ የመፍትሄ ሃሳቦችን ጠቁሟል።*

# ምስጋና

በቅድሚያ ከዚህ ላደረሰኝን ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይገባዉ፡፡ በመቀጠልም ውድ ጊዜያቸዉን ሰውተው፣ የጎደለዉን በመሙላት፣ ስህተቱን በማረም፣የተጣመመውን በማቃናትና ስደክም በማበርታት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በየደረጃዉ በማገዝ ይህን ቅርጽ እንዲይዝ እኔም ለዚህ ደረጃ እንድበቃ በማድረጋቸው ለአማካሪ መምህሬ ለግርማ ገብሬ (ዶ/ር) ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምስጋና ይድረሰው፡፡

በመቀጠልም መወለድ ቋንቋ ነው እንዲሉ ከጓደኝነት ይልቅ ወንድምነትህ በልጦ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቴን እንድጀምር ከማነሳሳት ጀምሮ በሃሳብና በምክር በማገዝ ዛሬ ላይ አድርሶኛልና ውድ ወንድሜ ሙሀመድ ሡኢድ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ እንዲሁም አጠቃላይ የሀሳብና የሞራል ድጋፍ ታደርጉልኝ የነበራችሁ ቤተሰቦቼ ለባለቤቴ ወ/ሮ አለምነሽ በየነ፣ ለልጆቼ ሰላምና ዳግም ወርቅነህ፣ለእህቴ ሙሉ ይርጋ ከጎኔ ስላልተለያችሁ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ በመቀጠልም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን አስተማማኝነት አረጋግጥ ዘንድ ፍቃድ ለሰጡኝ ለፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ጋሻዉ ጀንበሩ እና ጥናቱን ለማካሄድ ፍቃድ ከመስጠት ጀምሮ መረጃውን ሰብስቤ እስክጨርስ ዉድ ጊዜያቸውን በመሰዋታቸው ለፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት መምህራን ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

በመጨረሻም ለጥናቱ ውጤታማነት ይረዳ ዘንድ በቃለ መጠይቅ መረጃ ለሰጡኝና የንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ ምልከታ አንዳካሂድ ለተባበሩኝ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን መ/ር አቢዮት መሃሪ፣ መ/ርት ኸድጃ ዳዉድ እና መ/ር ሰለሞን ዘገየ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም ተመዝግበው በመማር ላይ የነበሩ የ9ኛ “B”፣ 9ኛ “C” እና 9ኛ “F” ክፍል ተማሪዎችም መረጃውን በትክክል እሰበስብ ዘንድ ለነበራችሁ ትዕግስት የተሞላበት ትብብር ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# ማውጫ


| ይዘት | ገጽ |
|---|---|
| አህጽሮተ ጽሁፍ | I |
| ምስጋና | II |
| ማውጫ | III |
| የሰንጠረዥ ማውጫ | V |
| **ምዕራፍ አንድ መግቢያ** | 1 |
| 1.1የጥናቱ ዳራ | 1 |
| 1.2የጥናቱ መነሻ ችግር | 3 |
| 1.3የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች | 5 |
| 1.4የጥናቱ ዓላማ | 5 |
| 1.5የጥናቱ አስፈላጊነት | 5 |
| 1.6የጥናቱ ወሰን | 6 |
| 1.7የጥናቱ ውሱንነት | 6 |
| 1.8የቁልፍ ቃላትና ጽንሰ ሀሳቦች ብያኔ | 6 |
| **ምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት** | 7 |
| 2.1. የንባብ ምንነት | 7 |
| 2.2. አንብቦ መረዳት | 8 |
| 2.3. አንብቦ መረዳትን ማስተማር | 8 |
| 2.4. በክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳትን ማስተማር | 9 |
| 2.5. አንብቦ መረዳትን የማስተማር ሂደት | 10 |
| 2.5.1የቅድመ ንባብ ተግባራት | 10 |
| 2.5.2የጊዜ ንባብ ተግባራት | 11 |
| 2.5.3የድህረ ንባብ ተግባራት | 11 |
| 2.5.4አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፈተናዎች ባህሪያት | 11 |
| 2.6.አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃዎች | 13 |
| 2.7.የጾታ ልዩነትና የቋንቋ ትምህርት | 14 |
| **ምዕራፍ ሦስት የአጠናን ዘዴ** | 16 |
| 3.1. የጥናቱ ንድፍ | 16 |
| 3.2. የጥናቱ ናሙና አመራረጥ | 16 |
| 3.2.1.የትምህርት ቤት አመራረጥ | 16 |
| 3.2.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ | 16 |
| 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች | 17 |

3.3.1.የአንብቦ መረዳት ፈተና 17
3.3.2.የክፍል ውስጥ ምልከታ 17
3.3.3.ቃለ መጠይቅ 18
3.3.4.የጥናቱ አካሄድ 18
3.3.5.የመረጃ አተናተን 20
**ምዕራፍ አራት የመረጃ ትንተና** 21
4.1. በፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና 21
4.2. የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ከጾታ አንጻር 26
4.3. በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና 29
4.4. የንባብ ትምህርት አተገባበርንና የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳትን በተመለከተ በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና 35
4.5 . የውጤት ማብራሪያ 37
**ምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳብ** 42
5.1.ማጠቃለያ 42
5.2.መደምደሚያ 44
5.3.የመፍትሄ ሃሳብ 45
ዋቢዎች 46
አባሪ “ሀ” 49
አባሪ “ለ” 53
አባሪ "ሐ" 57
አባሪ "መ" 58
አባሪ "ሠ" 59
አባሪ "ረ" 60

## የሰንጠረዥ ማዉጫ

**ሠንጠረዥ** 4.1. የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ውጤት (ደረጃ) ከፈተና አንድ አንጻር በድግግሞሽ መጠንና በመቶኛ ........................................................................22
**ሠንጠረዥ** 4.2. የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ውጤት (ደረጃ) ከፈተና ሁለት አንጻር በድግግሞሽ መጠንና በመቶኛ ........................................................................23
**ሠንጠረዥ** 4.3. የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል አጠቃላይ ውጤት (ደረጃ) በድግግሞሽ መጠንና በመቶኛ ........................................................................24
**ሠንጠረዥ** 4.4. የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት (One Sample t-test)........................................................................25
**ሠንጠረዥ** 4.5. የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል አጠቃላይ ውጤት ከጾታ አንጻር በድግግሞሽ መጠንና በመቶኛ ........................................................................26
**ሠንጠረዥ** 4.6. የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ከጾታ አንጻር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Sample t-test)........................................................................28
**ሠንጠረዥ** 4.7. የቅድመ ንባብ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ በምልከታ የተሰበሰበ መረጃ.30
**ሠንጠረዥ** 4.8. በምልከታ የንባብ ጊዜ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ የተሰበሰበ መረጃ.....32
**ሠንጠረዥ** 4.9. በምልከታ የድህረንባብ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ የተሰበሰበ መረጃ ....34

# ምዕራፍ አንድ፡ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች የተማሪዎችን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) ማጎልበትና ሁለቱን የእውቀት ዘርፎች (ሥነ-ጽሑፍና ሥነ-ልሳን) ማዳበር ነው። አጠኚውም ይሄንን እንደመነሻ በማድረግ የራሱን ጥረት አድርጓል። የአንብቦ መረዳት ውጤት ለአንድ ለተወሰነ የክፍል ደረጃ የሚዘጋጅ ምንባቡን በክፍል ደረጃው የተመደቡ ተማሪዎች ያለምንም ችግር ማንበብና መልዕክቱን መረዳት መቻላቸውን ይመለከታል (ጋሪሴት፣ 1981)።

እንደ ጋርሴት (1981) ማብራሪያ፣ ከንባብ ጠቀሜታዎች መካከል መረጃን ማግኘትና መዝናናት የሚገኙበት ሲሆን የሚነበበውን ነገር መገንዘብ ደግሞ የንባብ ዋነኛ ጉዳይ ነው። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ስኬታማ የንባብ ትምህርት እንደ ተማሪዎች የክፍል ደረጃ በይዘትና በአቀራረብ ተመጥኖ ይቀርባል። እንደ ክሮል (1996) ገለፃም፣ የማንበብ ተግባር ከተለያዩ ዓላማዎች አንፃር ይከናወናል። አንባቢያን የተለያዩ መረጃዎችን ለመፈለግ፣ ለመመርመር፣ አዲስ እውቀት ለመገብየትና ለመዝናናት ተግባር የተለያዩ ጽሑፎችን ሊያነቡ ይችላሉ። የማንበብ ተግባሩ ለየትኛውም ዓላማ ቢካሄድም ውጤታማ የሚሆነው አንባቢዎቹ ያነበቡትን ፅሑፍ በትክክል ትርጉም ሰጥተው ሲገነዘቡት ነው። አንብቦ መረዳት፣ የአንድን ፅሁፍ ሃሳብ መረዳትና በሚገባ መጨበጥን የሚገልፅ እሳቤ ሲሆን የፀሀፊውን ሐሳብ፣ መልዕክት፣ ስሜት ወዘተ... መለየትን፣ አውዳዊ ፍችዎችን መገንዘብንና ከአውድ ውጪ የሆኑ ፍችዎችን መረዳትን ያጠቃልላል (ጋሪሴት፣ 1981)። ስለሆነም የአንብቦ መረዳት ሂደት ፀሐፊው በፅሑፍ ውስጥ ለማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት በትክክል መረዳት መቻልን ይመለከታል።

ማንበብ በማንኛውም የትምህርት መስክ ስኬታማ ለመሆን ጠቃሚና ወሳኝ ክህሎት ነው። የተማሪዎች የማንበብ ችሎታና ክህሎት በየትኛውም ትምህርት ላይ ሂደታዊ የሆነ ለውጥ እንዲያመጡና ውጤታማነታቸው ላይ በጎ ተጽኖ ያሳድራል (ሀገር፣ 2017)። እንደ ላንዳሀ (2006) ገለጻ ደግሞ፣ ማንበብ ውስብስብ የሆነና ሰፊ ጊዜና በርካታ ልምምዶች የሚጠይቅ ክሂል ነው። በዚህም ማንበብ በቋንቋ መልክ የቀረቡ የህትመት መረጃዎችን የመቀበልና የመተርጎም ሂደትን ያካትታል።

በተመሳሳይ ካላ (2005) አንብቦ መረዳት የማንበብ ችሎታንና ብቃትን በመጠቀም ከተለያዩ የፅሁፍ ውጤቶች ውስጥ ዳራዊ እውቀትንና የቋንቋ ችሎታን መሰረት በማደርግ የተለያዩ

መረጃዎችን የማውጣትና የማዋሃድ ሂደትን የሚጠይቅ ተግባር መሆኑን ይገልጻሉ። በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡ ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው ማንበብ ለሁሉም የክፍል ደረጃዎች የሚዘጋጅ ምንባቡን በክፍል ደረጃው የተመደቡ ተማሪዎች ያለምንም ችግር ማንበብና መልዕክቱን መረዳት መቻልን የሚመለከት ሲሆን የራሱ የሆነ ዓላማና ጠቀሜታ ያለው ውስብስብ ተግባር ነው።

ንባብን በክፍል ውስጥ ማስተማር ሲባል የቃላት አነባበብን፣ የተዋጣለት የሀሳብ አገላለጽን፣ ጥርት ያለ የአነባበብ ድምፀትንና ሀሳብን ከፅሑፍ እንዲረዱ የማድረግ ሁኔታዎችን ሁሉ ያጠቃልላል (ናታል፣ 1982)። በድሉ (1996) እንደገለፁትም፣ ተማሪዎች የማንበብ ትምህርትን በክፍል ውስጥ ሲማሩ ሆህያትን አቀናጅተው ቃላትን፣ ከቃላት አሰካክተው ሀረጋትንና ዓረፍተ ነገርን በመመስረት ደረጃ በደረጃ ይማራሉ፤ የማንበብ ክሂላቸውን እያዳበሩ ሲሄዱም ወደ አንብቦ መረዳት ትምህርት ይሸጋገራሉ። በተመሳሳይም ናታል (1982) ተማሪዎች የማንበብ ክሂላቸውን እያዳበሩ ሲሄዱ ያለምንም እርዳታ በተገቢው ፍጥነት ከበቂ ግንዛቤ ጋር መልዕክትን አንብበው መረዳት ይችላሉ በማለት ያስረዳሉ። ለዚህም ይመስላል በሀገራችን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማንበብ ትምህርት "አንብቦ መረዳት" በሚል ይዘት የሚሰጠው።

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለአንብቦ መረዳት ክሂል የሚሰጠው ትኩረት ከሌሎች ክሂሎች አንጻር ሲታይ ከፍ ያለ ነው። የመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ከሚቀርቡት ልዩ ልዩ መልመጃዎች መካከል ትልቁን ድርሻ የሚወስዱት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ናቸው (በየነ፣ 1986)። ይሁን እንጂ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከክፍል ደረጃቸው አንጻር ሲነጻጸር ዝቅተኛ መሆኑን በዘርፉ የተሰማሩ ምሁራን በተደጋጋሚ የሚገልጹት ጉዳይ መሆኑን ተስፋዬ (1986)ን በመጥቀስ መኮንን (2000) ያስረዳሉ።

አንብቦ መረዳትን በማጎልበት ረገድ የሚካሄዱ ጥናቶች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ጠቀሜታቸው የጎላ መሆኑን ባለሙያዎች (ማረው 1998፣ በድሉ 1996) ይገልፃሉ። እንደ ባለሙያዎቹ ገለፃ፣ ጥናቶቹ ለቋንቋ ተማሪዎች፣ ለመምህራንና ለቋንቋ ባለሙያዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። ይኸውም ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ውጤታቸውን ለማሳደግ እንዲሁም ለመምህራንና ለቋንቋ ባለሙያዎች ውጤታማ የማስተማሪያ ዘዴ ለማመንጨትና የተማሪዎችን ውጤት ለማሳደግ ያግዟቸዋል።

ይህ ጥናትም በፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ክሂል ያለበትን ደረጃ ለመፈተሽ ሞክሯል፡፡

## 1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር

አንብቦ መረዳት፣ የአንድን ፅሁፍ ሃሳብ መረዳትና በሚገባ መጨበጥን የሚገልጽ እሳቤ ሲሆን የፀሃፊውን ሐሳብ፣ መልዕክት፣ ስሜት ወዘተ... መለየትን፣ አውዳዊ ፍችዎችን መገንዘብንና ከአውድ ውጪ የሆኑ ፍችዎችን መረዳትን ያጠቃልላል (ጋሪሴት፣ 1981)፡፡ ስለሆነም የአንብቦ መረዳት ሂደት ፀሃፊው በፅሁፍ ውስጥ ለማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት በትክክል መረዳት መቻልን ይመለከታል፡፡

እንደ ጋሪሴት (1981) ገለጻ፣ ከንባብ ጠቀሜታዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ መረጃን ማግኘትና መዝናናት ቢሆኑም የሚነበበውን ነገር መገንዘብ ግን የንባብ ዋና ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህም ስኬታማነት ንባብ እንደ ተማሪዎች የክፍል ደረጃ በይዘትና በአቀራረቡ ተመጥኖ ይሰጣል፡፡ እንደ ክሮል (1996) ገለጻም፣ የማንበብ ተግባር ከተለያዩ ዓላማዎች አንፃር ይከናወናል፡፡ አንባቢያን የተለያዩ መረጃዎችን ለመፈለግ፣ ለመመርመር፣ አዲስ እውቀት ለመገብየትና ለመዝናናት ተግባር የተለያዩ ጽሁፎችን ሊያነቡ ይችላሉ፡፡ ሆኖም የማንበብ ተግባሩ ለየትኛውም ዓላማ ቢካሄድም ውጤታማ የሚሆነው አንባቢዎቹ ያነበቡትን ፅሁፍ በትክክል ትርጉም ሰጥተው ሲገነዘቡት ነው፡፡

ንባብን በክፍል ውስጥ ማስተማር ሲባል የቃላት አነባብን፣ የተዋጣለት የሐሳብ አገላለጽን፣ ጥርት ያለ የአነባበብ ድምፀትን፣ ሐሳብን ከጽሑፍ እንዲረዱ የማድረግ ሁኔታዎችን ሁሉ ያጠቃልላል (ናታል፣ 1982)፡፡ በድሉ (1996) እንዳብራሩትም፣ ተማሪዎች የንባብ ትምህርትን በክፍል ውስጥ ሲማሩ ሆሄያትን አቀናጅተው ቃላትን፣ ከቃላት አሰካክተው ሐረግንና ዓረፍተነገርን በመመስረት ደረጃ በደረጃ ንባብን ይማራሉ፤ የንባብ ክሂላቸውን እያዳበሩ ሲሄዱም ወደአንብቦ መረዳት ትምህርት ይሸጋገራሉ፡፡ በተመሳሳይም ናታል (1982) ተማሪዎች የንባብ ክሂላቸውን እያዳበሩ ሲሄዱ ያለማንም እርዳታ በተገቢው ፍጥነት ከበቂ ግንዛቤ ጋር መልዕክትን አንብበው መረዳት ይችላሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡

ጃኔትና ቤቲ (1988) እንዳስረዱት፣ አንብቦ መረዳት ቃላዊ ከሆኑት ክሂሎች በተቃራኒው የበርካታ ችሎታዎች ቅንጅት ነው፡፡ እነሱም የቃላቱን ትርጉም መረዳት፣ ከዳራዊ እውቀትና ከተማረው ትምህርት ጋር ማያያዝ ናቸው፡፡ እንደ ሼንሀን (2006) ገለጻ ደግሞ፣ አንብቦ መረዳት በውስጡ ሁለት ደረጃዎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው የአንብቦ መረዳት ደረጃ በአገራችን አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል (ጌትነት 1990፣ ተሾመ 1997፣ ዘውዱ 1998፣ መኮንን 2000)፡፡ የጌትነት (1990) ጥናት በጋሞኛ ቋንቋ አፋቸውን በፈቱ የአርባ ምንጭ ሁለተኛ

ደረጃ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መዋቅር እውቀትና በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ጽሁፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ያካሄዱት ጥናት ነው። በጥናቱ ውጤት መሰረትም በጋሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ አፋቸውን ከፈቱ ተማሪዎች አንጻር ሲታዩ በአማርኛ ቋንቋ መዋቅር እውቀታቸውም ሆነ በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ጽሁፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ችሎታ ላይ እንደሚገኙ ተረጋግጧል። የተሾመ (1997) ጥናት በበኩሉ በደቡብ ኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በከምባታ ጠንባሮ ዞን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ችሎታ ላይ ያደረጉት ጥናት ነው። በጥናቱ ውጤት መሰረትም ተማሪዎች ከክፍል ደረጃው አኳያ በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ጽሁፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙና በንባብ ፍጥነታቸውም ዘገምተኛ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። በተመሳሳይ የዘውዱ (1998) ጥናት በትግረኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የአማርኛ አሃዶችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን የተመለከተ ነው። በጥናቱ ውጤት መሰረትም በትግረኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑ ተመልክቷል። የመኮንን (2000) ጥናት በበኩሉ በአዊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የተካሄደ ነው። በጥናቱ ውጤት መሰረትም በአዊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑ ተረጋግጧል።

ከላይ የቀረቡት ጥናቶች (ጌትነት 1990፣ ተሾመ 1997፣ ዘውዱ 1998፣ መኮንን 2000) አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ በመካሄዳቸው ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላሉ። ሆኖም ከላይ የቀረቡት ጥናቶች አንዳቸውም በፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ አልፈተሹም።

የዚህ ጥናት አቅራቢ በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ባገለገለባቸው 14 ዓመታት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች አማርኛ ቋንቋ ያስተማረና የአንብቦ መረዳት ችግር ያስተዋለ ቢሆንም ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ደረጃን በትክክል የፈተሹ ጥናቶችን አላገኘም። በተጨማሪም በአካባቢው አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ጽሁፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ነው፤ አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው በማለት አስተያየት ከመሰንዘር ያለፈ አንድም ጥናት ተካሂዶ አላገኘም። በመሆኑም አጥኚው የችግሩን ጥልቀት ደረጃ ማጥናት በቀጣይ ተማሪዎቹን ለይቶ ለማጥናት ያግዛል የሚል እምነት ያለው በመሆኑ ይህን ጥናት ለማካሄድ አነሳስቶታል።

## 1.3 የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች

ጥናቱ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ክሂል ያለበትን ደረጃ ለመፈተሽ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሯል፡፡ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች፡-

- ➢ በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ወንዶች ከሴቶች ያልተናነስን ማንበብ ይችላሉን?
- ➢ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከተማሪዎች ጾታ ጋር ዝምድና አለውን?
- ➢ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ምን ይመስላል?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ክሂልን መፈተሽ ነው፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ የሚከተሉት ሶስት ንዑሳን ዓላማዎች አሉት፡፡ እነርሱም፡-

- ➢ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ማሳየት፣
- ➢ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከተማሪዎች ጾታ ጋር ያለውን የተዛምዶ ደረጃ መግለጽ፣
- ➢ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብን መግለጽ የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት በዋናነት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ትክክለኛ መረጃ ይሰጣል፡፡ መረጃው ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ለተማሪዎችና ለተመራማሪዎች የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል፡፡

1. ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎቻቸውን አማርኛን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማሳየት፣የትምህርት አቀራረባቸውን፣የማስተማሪያ ስልታቸውንና እለታዊ የማስተማሪያ እቅዶቻቸውን ከተማሪዎች ችሎታ አንጻር እንዲያዘጋጁ ሊያግዝ ይችላል፡፡
2. ለተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ውጤት መሻሻል የሚያግዙ ተግባራትን ይጠቁማል፡፡
3. ወደፊት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ላይ ትኩረት አድርገው ሰፋ ያለ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች የመነሻ ሃሳብ በመስጠት አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ ከቦታ አንጻር በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በመተከል ዞን በፓዊ ወረዳ በፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ ብቻ ተካሂዷል፡፡ ምክንያቱም አጥኚው በመምህርነት ሙያ ላይ የሚገኝና ምርምሩን ከመደበኛ ማስተማር ስራው በተጨማሪነት የሚያካሂደው በመሆኑ ካለበት የጊዜ፣ የጉልበት፣ የገንዘብ፣ ወዘተ ችግር አንጻር ሌሎች ትምህርት ቤቶችን ለማካተት ስለሚቸገር ነው፡፡

ጥናቱ ከጊዜ አንጻርም በትምህርት ቤቱ በ2015 ዓ.ም ተመዝግበው የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ ተካሂዷል፡፡ የጥናቱ ዋና ዋና ተላውጦዎች የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና ጾታ ናቸው፡፡ ሆኖም ጥናቱ ሌሎች የክፍል ደረጃዎችን እና ጾታ ውጪ ያሉ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሌሎች ጉዳዮችን አያካትትም፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውሱንነት

ይህ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ለመፈተሽ በአንድ ወይም በፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሲሆን አጥኚው የአንብቦ መረዳት ፈተና፣ ቃለ መጠይቅና የክፍል ውስጥ ምልከታን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል፡፡

ይኸውም የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ደረጃ ለመፈተሽ ከሁለት ምንባቦች የተዘጋጀ ከእያንዳንዱ ምንባብ የወጡ 25 ጥያቄዎችን በድምሩ 50 ጥያቄዎች (የአንብቦ መረዳት ፈተና) እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡

ሆኖም አጥኚው ምንም እንኳ ከሁለት ምንባቦች የተዘጋጀ ከእያንዳንዱ ምንባብ የወጡ 25 ጥያቄዎችን በድምሩ 50 ጥያቄዎች (የአንብቦ መረዳት ፈተና) እንዲፈተኑ በማድረግ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ቢመዝንም ትክክለኛ መረጃ ላያስገኝ ይችላል፡፡ በመሆኑም ጥንቱ የአንብቦ መረዳት ውጤትን ለመፈተሽ በአንድ መሰናዶ ትምህርት ቤትና በአንድ የክፍል ደረጃ እንዲሁም በሁለት የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ብቻ ደረጃቸውን ወስኖ መናገሩ የጥናቱ ውሱንነት ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል፡፡

## 1.8 የቁልፍ ቃላትና ጽንሰ ሀሳቦች ብያኔ

በጥናቱ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላት የአንብቦ መረዳት ችሎታ፣ የንባብ ትምህርት አቀራረብ እና የአንብቦ መረዳት ችሎታና ጾታ ተዛምዶ ሲሆኑ አጠቃቀማቸውም እንደሚከተለው ነው፡፡

**የአንብቦ መረዳት ችሎታ፡-** በጥናቱ የተሳተፉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና የሚያስመዘግቡትን ውጤት ይመለከታል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት

## 2.1. የንባብ ምንነት

ማንበብ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ይበልጥ አስፈላጊና መሰረታዊ ከሆኑት ክሂሎች ውስጥ አንዱ መሆኑን ሌንደሲና ናይት (2006:70-71) ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም ንባብ በማንኛውም ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች እጅግ አስፈላጊ የሆነ ክሂል ነው፡፡ "የተማሪዎች ስኬትም ሆነ ውድቀት የሚወሰነው በሚኖራቸው የግል የማንበብ ክህሎት ወይም ችሎታ ነው፡፡" በማለት ኔልሰን (1963:18) ያስረዳሉ፡፡ "ንባብ በአንድ ጽሁፍ አማካኝነት የሰፈረውን መልእክት መረዳትና ማገናዘብን ይመለከታል፡፡ እንዲህ ስለተባለ ግን መልእክቱ በጽሁፍ አማካኝነት በቀላሉ ሰፍሮ የሚገኝ አለመሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ በጽሁፍ የሰፈረውን መልእክት ለመረዳትም የአንባቢን ንቁ የአእምሮ ተሳትፎ ይጠይቃል" በማለት አለም /1997፣2/ ይገልፃሉ፡፡

ስለንባብ ምንነት አልደርሰን (2000:3) እንደገለፁት፣ ንባብ ከተፃፈ ጽሁፍ ላይ መረጃ መውሰድ ብቻ ነው ብሎ ወስኖ መግለጽ ያስቸግራል፡፡ ይኸውም አንድ አንባቢ የሚያነበው ለተለያየ ዓላማ ነው፤ በመሆኑም ከዓላማው አንፃር የተለያዩ ውህድ ክሂሎችንና ስትራቴጂዎችን ሊጠቀም ይችላል፡፡ ስለዚህ ንባብ ለእውቀት /ለመረዳት/ ተብሎ ብቻ የሚተገበር ሳይሆን እንደ አንባቢው ዓላማ ለተለያዩ ተግባራት የሚከወን በመሆኑ በውስጡ ሌሎች ንኡሳን ክሂሎችን አካቶ የያዘ ችሎታ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአንባቢውን የቋንቋ ብቃት የሚለካ ክሂል ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

እንደ ሜይ (1990፡10) አገላለፅ የንባብ ምንነት ከተለያዩ ነጥቦች አንፃር ሊገለጽ ይችላል፡፡ ይኸውም፡-

- ንባብ በጽሁፍ የቀረበውን ሀሳብ የመረዳት ሂደት ነው፡፡
- ንባብ የመተርጎም፣ ፍቺ የማፈላለግና በጽሁፍና በስዕል የቀረቡ መልዕክቶችን ወደ ግል ግንዛቤ የመተርጎም ሂደት ነው፡፡
- ንባብ አንባቢው በጽሁፍ ከቀረቡ ቃላት ጋር የሚያደርገው ጭውውትም ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ አገላለጽ አንድን ጽሁፍ ለመረዳት በሚደረግ ሂደት አንባቢ ከቃላት ጋር በመነጋገርና በመጨዋወት የጸሀፊው ሀሳብ ይህ ሊሆን ይችላል በሚል ግምት የሚያከናውነው ተግባር ነው፡፡

በተጨማሪም ጋርሌት (1981፡8) "ንባብ ማለት መገመት፣ መተንበይ፣ ማመሳከር፣ ራስን ጥያቄ መጠየቅንና ንቁ ተሳትፎ ማድረግን የሚፈልግ ሂደት ነው፡፡" በሂደቱም አንባቢ ከምንባቡ አውድ በመነሳት የአዳዲስ ቃላት ፍቺዎችን የሚገምትበት ገና ከመነሻው ባገኘው

መረጃ ላይ በመመርኮዝ የምንባቡን ዋና ይዘትና ወደፊት ምን እንደሚገጥመው የሚተነብይበት፣ ያነበበውን ፅሁፍ መረዳት አለመረዳቱን ራሱን ጥያቄ በመጠየቅ የሚያመሳክርበት ሂደት መሆኑን እንረዳለን በሌላ በኩል የተለያዩ ምንባቦችን ሲያነብ የተለያዩ ችሎታዎችንና ስልቶችን መጠቀም እንዳለበት እንገነዘባለን፡፡

በአጠቃላይ ስለንባብ ምሁራን ወጥ የሆነ ብያኔ ያልሰጡበት ምክንያት ከንባብ ባህሪ የመነጨ እንደሆነ አልደርሰንና ኧርጋርት (1984፡1) ይገልጻል፡፡ ይኸውም የንባብ ትግበራ ግላዊና ረቂቅ መሆኑ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን ያደረገው የተለያዩ አንባቢዎች አንዲን ጽሁፍ የሚረዱበት መንገድ፣ የሚያነቡበት ዓላማና የአነባበብ ዘዴያቸው የተለያየ መሆን ነው፡፡ ንባብ ማለት አንድን የሚፈለግን መረጃ ብቻ ነቅሶ ማውጣት ሲሆን ለሌላው ደግሞ መልዕክቱን በዝርዝር መገንዘብ ይሆናል፡፡ እንዲሁም ንባብ ጸሀፊው በጽሁፉ ላስተላለፈው መልዕክት አንባቢ ምላሽ የሚሰጥበት ተግባር የሚሆንበት ሂደትም አለ፡፡

## 2.2. አንብቦ መረዳት

አንብቦ መረዳት በማንበብ ትምህርት ውስጥ ወሳኙ ተግባር ነው፡፡ ማንኛውም አንባቢ በንባብ ተግባር ውስጥ የሚገባው አንብቦ ለመረዳት ነው (ፒኩልስኪና ቻርድ፣ 2005)፡፡ እንደ ፒኩልስኪ እና ቻርድ፣ (2005) አገላለጽ፣ አንብቦ መረዳት ትርጉም ያለው ግንዛቤና መልዕክት ለማግኘት አንባቢው ከሚያነበው ጽሁፍ ጋር የሚያደርገው የሀሳብ ልውውጥ የማሰላሰል መስተጋብራዊ ግንኙነት ነው፡፡ የአስተሳሰብ አድማስን ስለሚያሰፋ፣ ሁለገብ ዕውቀት ስለሚያላብስና በራስ መተማመንን ስለሚያጎለብት ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል (ዳዊት፣ 2008)፡፡ ማንኛውም ሰው ማወቅ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ሊያገኝ ከሚችልባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው ንባብ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የጠለቀ ዕውቀት እንዲኖራቸውና በዚህም በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ከሚያስፈልጓቸው መሰረታዊ ክሂሎች መካከል አንዱ የአንብቦ መረዳት ክሂል ነው፡፡

## 2.3. አንብቦ መረዳትን ማስተማር

አንብቦ መረዳት በጽሑፍ ሊተላለፍ የሚፈለግን መልዕክት የመገንዘብ ሂደት ነው፡፡ እንደ ኑር (1996) ገለጻ፣ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ አንብበው በቀላሉ እንዲረዱ የሚቀርበው ምንባብ የቋንቋ ይዘት የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ከግንዛቤ ያስገባ መሆን አለበት፡፡ አልደርሰንና አርግሃርት (1984) በበኩላቸው፣ የአንብቦ መረዳት ትምህርት የታለመለትን ግብ እንዲመታ መምህሩ በቅድሚያ የቀረበው ምንባብ ከተማሪዎች ዕውቀት እና ክህሎት እንዲሁም ማህበራዊ ዳራ ጋር የሚጣጣም መሆኑን መፈተሽ አለበት በማለት ሃሳቡን ያጠናክሩታል፡፡ አንድ መምህር እነዚህን ጉዳዮች በቅድሚያ የቀረበው ይዘት

ከተማሪዎች የቀደመ እውቀት ጋር መጣጣሙን ካረጋገጠ በኋላ አንብቦ መረዳትን ማስተማር ይችላል፡፡

ሀርመር (1991) እንደሚያብራሩት የአንብቦ መረዳት ክህሎት ትምህርት በሚከተለው መንገድ ሊቀርብ ይችላል፡፡

❖ **የቃላት ፍቺን ማስገንዘብ፡-** ተማሪዎች በምንባቡ የቀረቡትን ቃላት አውዳዊና አገባባዊ ፍቻቸውን እንዲረዱ ማድረግ ይገባል፡፡ የቃላትን ፍቺ ሲባልም የአውዳዊ ፍቺን ማስረዳት/ማስገንዘብ ነው፡፡

❖ **የምንባቡን ግልጽ መልዕክት ማስገንዘብ፡-** በምንባቡ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠ መልዕክት ለማብራራትና አጽኖት ለመስጠት የገቡትን ሐሳቦች ማስገንዘብ ይመለከታል፡፡

❖ **የምንባቡን ድብቅ መልዕክት ማስረዳት፡-** በምንባቡ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠውን መልዕክት መነሻ በማድረግ በአንድምታ የተቀመጠውን (ድብቁን) መልዕክት እንዲረዱ ማድረግ ነው፡፡

❖ **የምንባቡን የሐሳብ ፍሰት ማስገንዘብ፡-** ተማሪዎች የምንባቡን ቅደም ተከተል፣ የሐሳብ ፍሰት፣ የሐሳቦችን ቅንብርና ዝምድና መገንዘብ ይገባቸዋል፡፡ ይህም በአረፍተ ነገሮችና አንቀጾች ቅደም ተከተላዊ ውህደትና ዝምድና ሊገለጽ ይችላል፡፡

❖ **ሰዋስዋዊ አገባብ እና ትርጉም ማስገንዘብ፡-** ተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ የሚያገኙትን አያያዥ ቃላትና ሐረጋት ያላቸውን ሰዋስዋዊ አገባብና ትርጉም ማወቃቸው የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ በቀላሉ እንዲገነዘቡ ያግዛቸዋል፡፡

## 2.4. በክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳትን ማስተማር

አንብቦ መረዳት ውስብስብ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም አንብቦ መረዳትን ማስተማር ሲባል አንድን የቋንቋ ክሂል ለማዳበር ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ክሂሎች በተጓዳኝ የምናስተምርበት፣ ማህበራዊ፣ ሳይንሳዊና ስነ-ልቦናዊ ዕውቀቶችን የምናስጨብጥበት በመሆኑ በመማር ማስተማር ሂደቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል (ጆርዳን፣ 1993)፡፡ ዊሊያምስ (1984) እንደገለጹትም፣ አንብቦ መረዳትን በክፍል ውስጥ ለማስተማር የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይጠቅማል፡፡

➢ ተማሪዎች እንዲያነቡት የቀረበው ምንባብ የሚያጓጓ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች ታሪኩን አንብበው ለመረዳት የሚፈጥረው መነሳሳት የንባብ ፍጥነታቸውን እና ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ ያስችላቸዋል፤

➢ ምንባቡን አስመልክቶ ማንኛውም ዓይነት ውይይትና ጥያቄ ለተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ ማድረግ ያስፈልጋል፤

- ለተማሪዎች የሚቀርበው ምንባብ እና የመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ሊያዳብር በሚችል መልኩ መዘጋጀት አለበት፤
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከናወነው የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎችን ሊለውጥና ሊያሳውቅ በሚችል፣ በተግባር የታገዘ፣ ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሳትፍ በሚችል መልኩ መሆን አለበት፤
- በአንብቦ መረዳት ትምህርት ወቅት መምህሩ መረጃ ከመስጠት፣ ስለምንባቡ መጠነኛ ገለጻ ከመስጠት፣ የክፍሉን የመማር-ማስተማር ሂደት ከመቆጣጠር፣ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ከመስጠት ያለፈ ተግባር ማከናወን የለበትም፤
- ተማሪዎች የሚማሩት የአንብቦ መረዳት ትምህርት በክፍል ውስጥ ብቻ የሚቀር ሳይሆን ከክፍል ውጭም ወጥተው ሊተገብሩት የሚያስችል ተነሳሽነትና ተጨባጭ እውቀት ሊፈጥር እና ሊያስጨብጥ በሚችል መልኩ መሆን አለበት፤
- ተማሪዎች ከሚያነቡት ምንባብ መረጃዎችን ከመውሰድ በአለፈ ውይይቶችን እንዲያካሂዱ፣ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንዲያነሱ ማስቻል አለበት፤
- ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ከሚያነቡት ቅንጫቢ በአለፈ ከመማሪያ ክፍል ውጭም ሰፊ ንባብ እንዲያካሂዱ በሚያነሳሳ መልኩ መሆን አለበት፡፡

## 2.5. አንብቦ መረዳትን የማስተማር ሂደት

አንብቦ መረዳትንም በክፍል ውስጥ ለማስተማር ልንከተላቸው የሚገቡ ተግባራት ሦስት ናቸው፡፡ እነሱም፡- ቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜና ድህረ ንባብ ተግባራት ናቸው፡፡

### 2.5.1 የቅድመ ንባብ ተግባራት

ተማሪዎቹ ስለሚያነቡት ነገር ጉጉት እንዲኖራቸውና ለንባብ እንዲነሳሱ የሚያደርጓቸው ናቸው፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎቹ የያዙዋቸውን ፍንጮች ከሚነበበው ምንባብ ጋር እንዴት ማዛመድ እንዳለባቸው የሚያሰላስሉበት ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል፡፡

ስለምንባቡ ግምት እንዲኖራቸው አጠቃላይ በሆነ ነገር መጀመር ውጤታማ ያደርጋል፡፡ ይህም ማለት የተለያዩ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት የምንባቡን ፍንጭ መስጠት ይቻላል፡፡ ተከታዮቹን ዓይነት ጥያቄዎች ማዘጋጀት ደግሞ ሂደቱን የበለጠ ውጤታማ ያደርጋል፡፡

- የቃላት ፍቺን መጠየቅ
- ግምት ሰጪ ጥያቄዎች ማቅረብ
- ምንባቡን በጥቅሉ ማስተዋወቅ

### 2.5.2 የጊዜ ንባብ ተግባራት

በዚህ ጊዜ የተማሪዎቹ ተግባር የሚሆነው እያሳጠሩ በማንበብ መልስ የሚሰጥባቸውን ጥያቄዎች መመለስ ይሆናል፡፡ በቅድመንባብ የጨበጧቸውን ግንዛቤዎችና የያዙዋቸውን ግምቶች የሚያረጋግጡባቸውን ጥያቄዎች የሚሰሩባቸው ይሆናል፡፡ ምንባቡን አንብበው ጥያቄዎቹን ሲመልሱ ከመጀመሪያው ግምታቸው ጋር የተመሳሰለ ወይም የተለያየ መሆኑን እንዲያስቡበት ማሳሰብም ለንባብ ጠቀሜታ እንዳለው ይታመናል፡፡ በተጨማሪም ሊያውቁ ስለፈለጉት ነገርም በቂ ግንዛቤ ማግኘት አለማግኘታቸውንም መጠየቁ ምንባቡን ስለ መረዳታቸው የሚጠቅም ነው፡፡ በንባብ ጊዜ ተማሪዎቹ በተለያዩ ተግባራት ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነሱም፡-

- የቃላትን አውዳዊ ፍች መፈለግ
- የምክንያትና የውጤት ተያያዥነትን መጠየቅ

### 2.5.3 የድህረ ንባብ ተግባራት

ይህ ደረጃ በአብዛኛው የግምገማ ስራዎችን የሚይዝ ነው፡፡ ምንባቡን መነሻ በማድረግ ከክፍል ውጪ ካለው ዓለም ጋር በማዛመድ ሐሳብ ሊያቀርቡባቸው የሚያስችሏቸው ጥያቄዎች የሚካተቱበት ነው፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎቹ ከራሳቸው ህይወትና ልምድ አኳያ ፍርድ የሚሰጡበት፣ የአስተሳሰብና የአመለካከት አድማሳቸውን ነፃነት ተጠቅመው ሐሳብ የሚሰነዝሩበት ነው፡፡ በዚህም የክሂሎች ቅንጅት አመዛዝኖ ሊታይ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡-

- ምንባቡን ወደሃዋል? ለምን?
- ጽሑፉ ለምን የተፃፈ ነው?
- ስላነበባችሁት ጉዳይ ያላችሁን አስተያየት ግለፁ፡፡
- ለዚህ ምንባብ ማጠናከሪያ የሚሆን ምሳሌ ማቅረብ ትችላላሁ? ወዘተ....

### 2.5.4 አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፈተናዎች ባህሪያት

አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የሚዘጋጁ ጥያቄዎች ምንባቡ ከቀረበበት ቋንቋ ጠንከር የሚል መሆን የለበትም፡፡ ከምንባቡ የሚወጡ ጥያቄዎች ግልጽና ቀላል በሆነ ቋንቋ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመፈተን የሚቀርቡ ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች መያዝ አለባቸው፡፡ እንደ አለም (1995፡12-13) አገላለጽ የአንብቦ መረዳትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጥያቄዎች በጽሁፍ ወይም በቃል ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ አቀራረባቸውም አጭር መልስ እንዲሰጡ በማድረግ፣ በክፍት አጠያየቅ፣ በምርጫ ወይም በእውነት ሐሰት በል በሚል መልኩ ሊሆን ይችላል፡፡ ጥያቄዎቹ የሚቀርቡበት መንገድ

የተለያየ ሊሆን ቢችልም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ግን ግብ መቺ መሆን እንዲችሉ የሚከተሉትን ነጥቦች መሰረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

1. ጥያቄዎቹ ምንባቡን ባላነበበ ሰው ሊመለሱ የሚችሉ ሊሆኑ አይገባም፡፡
2. ጥያቄዎቹ በአንድ በተወሰነ የምንባቡ ክፍል ላይ የተመሰረቱ ሳይሆኑ ሁሉንም የምንባቡን ክፍል በሚዳስሱበት መንገድ የሚዘጋጁበት ሁኔታ ሊመረመር ይገባል፡፡
3. የጥያቄዎቹ ቁጥር እጅግም ሳይበዛ እጅግም ሳያንስ በቂ የሆነ መጠን እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡
4. የተለያዩ የአንብቦ መረዳት መልመጃ የማቅረቢያ መንገዶች አሉ፡፡ ስለዚህም ጥያቄዎቹን በተለያየ አቀራረብ መንገድ ለማቅረብ መሞከር አስፈላጊ ይሆናል፡፡
5. ጥያቄዎቹ አንድ አንባቢ ሊኖረው ከሚገባው የንባብ ስትራቴጂ ጋር የማስተዋወቅ ባህል ሊኖራቸው ይገባል፡፡
6. ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ ምንባቡን በበለጠ እንዲረዱ የሚያግዙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
7. ጥያቄዎቹ የተገለጹበት ቋንቋ ከምንባቡ ቋንቋ የጠነከረ ወይም የከበደ መሆን የለበበትም፡፡
8. የጥያቄዎቹ መልሶች ተማሪው በደረጃው ሊኖረው ከሚገባው የቋንቋ ብቃት የሚልቅ የቋንቋ አጠቃቀም መጠየቅ የለባቸውም፡፡
9. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የተማሪውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍ ሊያደርጉ በሚችሉበት መንገድ እንጂ የተማሪውን ችሎታ የሚፈትኑ ዓይነት ሆነው መቅረብ አይኖርባቸውም፡፡
10. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር ተጣምረውና ተቀናጅተው የሚቀርቡበትን መንገድ ማፈላለግ አስፈላጊ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከተመረጡት ምንባቦች ጥያቄዎች በሚወጡበት ጊዜ ምንባቡን በጥንቃቄ በማንበብ ዋና ዋና ሀሳቦችን፣ መረጃዎችን፣ ነጥቦችን፣ ምሳሌዎችን ወዘተ. በማስታወሻ በመያዝ ለጥያቄ ማውጫ መጠቀም ይቻላል፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና በሚጻፍበት ወቅት የሚከተሉትን ነጥቦች ከግንዛቤ ማስገባት እንዳለብን ሄጅ (1989፡130) እና ማድሰን (1983፡ 83-84) ይገልጻሉ፡፡

1. ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ የምንባቡን ሀሳብ ሳይረዱ ወይም ሳይገነዘቡ ወይም ምንባቡን ሳያነቡ የሚመልሷቸው መሆን የለባቸውም፡፡
2. የጥያቄዎቹ መልሶችም በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ወይም በምንባቡ መሠረት የሚመለሱ ሊሆኑ ይገባል፡፡

3. አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የምንጠቀማቸው ምዘናዎች ከተወሰነ ባህል ጋር የተሳሰሩ መሆን የለባቸውም፡፡ ባህልን የምንፈትን ካልሆነ፡፡
4. እንዲሁም ጥያቄዎቹ ከምንባቡ እንዳለ ቃል በቃል ተወስደው የቀረቡ መሆን የለባቸውም፡፡ ነገር ግን በቀላልና ግልጽ ቋንቋ መጻፍ አለባቸው፡፡
5. አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የምናዘጋጀው ፈተና ከቋንቋ ክሂል ውጭ በሆነ እውቀት የሚመለስ መሆን አይኖርባቸውም፡፡

## 2.6. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃዎች

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን መስፈርቶች አስቀምጠዋል፡፡ እንደ ሄጅ (1989:119) ገለጻ አንድ ጽሁፍ የያዘውን ሀሳብ ወይም መልዕክት ተፈታኞች ሙሉ በሙሉ ተረድተውታል ለማለት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በሙሉ መመለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ነገርግን የሰው ልጅ አዕምሮ በጽሁፍ የቀረቡ ሀሳቦችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመመልከት የሚገነዘብ በመሆኑ የአንብቦ መረዳት ፈተና ተፈታኞች ከ80 በመቶ በላይ ውጤት ካስመዘገቡ የቀረበውን ጽሁፍ ተረድተውታል ማለት እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡

ምክንያቱም ለማንበብ ፍጥነቱም ሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታ የተለያዩ አንባቢዎች በተለያየ ፍጥነትና የመረዳት ችሎታ ደረጃ የሚያነቡ ስለሆነና እሳቤዎቹም በአንጻራዊነት የሚገልጹ ስለሆነ የደረጃ መስፈርቱ ከፍ ሲል በተገለጸው መሰረት (80 በመቶ) ቢቀመጥ የተሻለ እንደሚሆን ባለሙያው ያስገነዝባሉ፡፡

በሌላ በኩል ማድሰንና ሌሎች (1983:91) ተማሪዎች ከበቂ ፍጥነት ጋር በተሰጣቸው የችሎታ መለኪያ ፈተና ያመጡት ውጤት ከ40% በታች ከሆነ በጣም ዝቅተኛ፣ ከ50-41% ዝቅተኛ፣ ከ69-51% መካከለኛ፣ ከ70-80% በቂ፣ 81% እና ከዚያ በላይ ከሆነ ደግሞ ከፍተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አላቸው በማለት ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ፍጥነት እንደ አንባቢዎች የሚለያይ ስለሆነ ነው፡፡

ናራያንስዋሚ (1975፡144-147) ደግሞ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤትን ሲገልጹ ከ10 ከታረመ ፈተና ከ9-10 ውጤት ያስመዘገቡ ከፍተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው፣ ከ7-8 ያስመዘገቡ በቂ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው፣ ከ5-6 ያስመገዘቡ ዝቅተኛ እና ከ5 በታች ያስመዘገቡ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ የሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተብለው እንደሚፈረጁ ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ ስንመለከት በተለይ አማካይ ችሎታ ያላቸውን ተፈታኞች በተመለከተ የመቀራረብ ሁኔታ መኖሩን መገንዘብ ይችላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ከ10 ከታረመ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ከ9-10

ያገኙ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው፣ በፈተና ውጤቱ ከ7-8 ያገኙ በቂ ችሎታ ያላቸው ሲሆኑ በአንጻሩ ከ5 እስከ 6 ውጤት ያገኙ ዝቅተኛ ችሎታ ያላቸው እና ከ5 በታች ውጤት ያገኙ በጣም ዝቅተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው ተደርገው ተወስደዋል፡፡ ይህ የደረጃ መስፈርት የተፈታኞችን የችሎታ ደረጃ ለመመዘን የተሻለ እንደሚሆን በአጥኚውና በሌሎች መምህራን ታምኖበታል፡፡

## 2.7. የጾታ ልዩነትና የቋንቋ ትምህርት

በአዕምሯዊ ተግባራት ረገድ በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚኖር ልዩነትን አስመልክቶ መጠነ ሰፊ ጥናት ያካሄዱት ማኮቢና ጃክሊን (1974) በቃላዊና ስነልሳናዊ ጥናቶች ሴቶች ከወንዶች የተሻለ አማካይ ውጤት ሲያስመዘግቡ፣ በአንጻሩ በሂሳብና በሙያና ቴክኒክ ችሎታዎች የወንዶች አማካይ ውጤት በልጦ ተገኝቷል፡፡ ይሁን እንጂ የተጠቀሱት ተመራማሪዎች "ቃላዊ ተግባራት" የሚለው ሀረግ ለያዘው ጽንሰ ሀሳብ ግልጽ የሆነ ብያኔ ለመስጠት ባለመቻላቸው የጥናታቸው ውጤት አጠራጣሪ መሆኑን ዋሪክና ናግሊየር (1993) ይጠቅሳሉ፡፡ በሌላ በኩል ምንም እንኳን ማኮቢና ጃክሊን በቃላዊ ተግባራት ረገድ ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ ሆነው መገኘታቸውን ቢጠቁሙም የታየው ልዩነት ግን እጅግ አነስተኛ መሆኑን ዘግበዋል፡፡

ዊሊያምስ (1985) የተለያዩ ምሁራንን ጠቅሰው እድሜያቸው ከ 9 ወር እስከ 12 ዓመት በሚደርስ ወንድና ሴት ልጆች መካከል ያካሄዳቸው ጥናቶች አጠቃላይ ሁኔታ በቋንቋ መልመድ/መማር ረገድ ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ ሆነውም መገኘታቸውን የሚያሳይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሱት ግኝቶች በማናቸውም የእድሜ ደረጃ ሴት ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት፣ በቃላት እውቀት መጠን፣ በንባብ ክሂል ወዘተ ከወንዶች የተሻሉ መሆናቸውን የሚያመለክቱ መሆናቸውን እንደሆኑ ያስረዱ ሲሆን፣ ኦልሰን (1979) በበኩላቸው በየትኛውም የእድሜ ደረጃ ላይ በንባብ ክሂል ረገድ ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ ሆነው መገኘታቸውን አረጋግጠዋል፡፡ ቤትዝ እና ፊትዝጀራልድም (1987) ከዚህ አኳያ ሴቶች የተሻሉ መሆናቸውን የሚያሳዩ በርካታ መረጃዎች መኖራቸውን የሚያመለክቱ ሲሆን ባንክ ቢድልና ጉድ (1980) በበኩላቸው እንደጠቀሱት በተለይም በአሜሪካ ከ 1909 ጀምሮ የተከናወኑ በርካታ ጥናቶች ግኝት በተከታታይ እንደሚያሳየው በንባብ ክሂል ሴቶቹ ከወንዶቹ የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ተመራማሪዎች እንደሚጠቁሙት ንባብን የሴቶች ተግባር እንደሆነ የመቁጠር አዝማሚያም በአብዛኛው የሚታይ ሲሆን (ባንክ ቢድልና ጉድ 1980፣ ዊሊምስ 1985፣ ቤትዝ እና ፊትዝ ጀራልድ 1987) የዊሊያምስ ጥናት ግኝት እንደሚያመለክተው ንባብን የሴቶች

ተግባር አድርገው ከሚመለከቱት ይልቅ ይህን መሰሉ አመለካከት የሌላቸው ወንዶች የተሻለ የማንበብ ችሎታ ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ቤትዝና ፊትዝጀራልድ (1987) በበኩላቸው ንባብ ለወንዶች ተገቢ የሆነ ክንዋኔ መሆኑ በሚታመንባቸው እንደ እንግሊዝና ጀርመን በመሳሰሉ ሀገሮች ውስጥ ወንዶቹ ከሴቶች የተሻለ የማንበብ ችሎታ እንዳላቸው ይጠቁማሉ፡፡

በአንጻሩ በንባብ ክሂል ረገድ በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነት የሌለ መሆኑን የሚጠቁሙ የጥናት ግኝቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ሆካይዶ በተባለች የጃፓን ደሴት ውስጥ ኬጋን የተባለ ተመራማሪ ባካሄደው ጥናት በዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ላይ ይማሩ በነበሩ ወንዶችና ሴት ተማሪዎች መካከል በንባብ ክሂል ረገድ ምንም ልዩነት አለማግኘቱን የጠቆመ ሲሆን በእስራኤል ሀገር የተደረጉ ሌሎች ምርምሮችም በወንዶችና በሴቶች የንባብ ችሎታ ረገድ ምንም ልዩነት አለመታየቱን መግለጻቸውን እና ይህም የማህበረሰቡ ለሴቶችናለወንዶች ከሚሰጠው እኩል የሆነ ኃላፊነት ጋር ተዛምዶ ሊኖረው እንደሚችል ተመራማሪዎቹ መጠቆማቸውን ጭምር ባንክ ቢድልና ጉድ (1980) ዘግበዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የአጠናን ዘዴ

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

ጥናቱ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታን የሚፈትሽ ነው፡፡ የጥናቱ ንድፍ ከመጠናዊ ምርምር የሚመደብ ሲሆን ገላጭ የምርምር ስልትን ተከትሎ ተካሂዷል፡፡ የጥናቱ ዋና ዋና ተላውጦዎች የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ውጤት እና ጾታ ናቸው፡፡

### 3.2. የጥናቱ ናሙና አመራረጥ

#### 3.2.1. የትምህርት ቤት አመራረጥ

ጥናቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመፈተሽ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በመተከል ዞን ስር ከሚገኙት ሰባትት ወረዳዎች መካከል በፓዊ ወረዳ ላይ ተካሂዷል፡፡ ይህም ተማሪዎች ከአማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ጋር ተቀላቅለው የሚገኙበት በመሆኑ ነው፡፡ በፓዊ  ወረዳ ሰባት መሰናዶና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ ቀጠና ሁለት መንደር ሰባት መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ ቀጠና ሁለት መንደር ሁለት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ቀጠና ሁለት መንደር 49 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ህዳሴ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ቀጠና ሁለት መንደር 14 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ እና ቀጠና ሁለት መንደር 23/45 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች) ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ትምህርት ቤቶች መካከልም አጥኚው የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመፈተሽ ፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት በአመቺ ንሞና ዘዴ ተመርጧል፡፡ ሌሎች ትምህርት ቤቶችን ቢያካተት መረጃውን በትክክል ለመሰብሰብ ስለሚቸገር መረጃውን በቀላሉ ለመሰብሰብ ይረዳዋል ተብሎ በመታመኑ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤትን በአመቺ ንሞና ዘዴ በመምረጥ ጥናቱን አካሂዷል፡፡

#### 3.2.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ

ጥናቱ በፓዊ ወረዳ ፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመፈተሽ በ2015 ዓ.ም በትምህርት ቤቱ ተመዝግበው በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመፈተሽ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም ተማሪዎቹ ወደ ትምህርት ቤቱ አዲስ የመጡ በመሆናቸው ያላቸውን

ትክክለኛ የአንብቦ መረዳት ደረጃ ለማወቅ ስለሚረዳ ነው፡፡ ሆኖም የ10ኛ፣ የ11ኛና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ሰፊ ግንኙነት ያደረጉና ቀድመው ወደ ትምህርት ቤቱ የመጡ በመሆናቸው በጥናቱ ውስጥ አልተካተቱም፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በፓዊ  መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመፈተሽ ዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴን በመጠቀም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ ተካሂዷል፡፡

በመሆኑም በትምህርት ቤቱ ከሚገኙት ሰባት የዘጠነኛ መማሪያ ክፍሎች መካከል ሶስት መማሪያ ክፍሎች የእጣ (ሎተሪ) ንሞና ዘዴን በመጠቀም ዘጠነኛ 9ኛ "B"፣ 9ኛ "C" እና 9ኛ "F" ተመርጠዋል፡፡ በመሆኑም በተጠኚ መማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ 99 ወንድ እና 95 ሴት በድምሩ 194 ተማሪዎች በመረጃ ምንጭነት ተሳትፈዋል፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ጥናቱ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመፈተሽ ሶስት የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ተጠቅሟል፡፡–እነርሱም የአንብቦ መረዳት ፈተና፣ የክፍል ውስጥ ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.3.1. የአንብቦ መረዳት ፈተና

ጥናቱ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለመመርመር መረጃዎች በአንብቦ መረዳት ፈተና ተሰብስበዋል፡፡ ይሄውም ጥናቱ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመገምገም ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች በአጥኚው ተዘጋጅቶ ሶስት በአማርኛ ቋንቋ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪ ባላቸው መምህራን ተገምግመው እንዲሁም በአማካሪ መምህሩ አስተያየት ተሰጥቶባቸው ተማሪዎቹ እንዲፈተኗቸው ተደርጓል፡፡

በዚህም ጥያቄዎቹ ለፈተና በቀረቡት ሁለት ምንባቦች ላይ ብቻ ተመስርተው የተዘጋጁ የምንባቡን አጠቃላይ ሃሳብ፣ ዝርዝር ሃሳቦች፣ የተፈለገ ውስን መልዕክትን ለይቶ ማውጣትን፣ የቃላት አውዳዊ ፍችን፣ የቃላት ቀጥተኛ ፍችን፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን እና ምሳሌያዊ አባባሎችን መልዕክትን መረዳትን እንዲያጠቃልሉ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሰረት ተማሪዎቹ ከቀረቡላቸው ሁለት ምንባቦች ከእያንዳንዱ ምንባብ የወጡ 25 ጥያቄዎችን በድምሩ 50 ጥያቄዎች እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡

### 3.3.2. የክፍል ውስጥ ምልከታ

በጥናቱ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብን ለመግለጽ ይረዳ ዘንድ የክፍል ውስጥ ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ

ውሏል። ይሄውም በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ትምህርትን ለማስተማር የቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜ እና የድህረ ንባብ ትምህርት አቀራረብን በሚመለከት የተዘጋጀ የምልከታ ቅጽ ጥቅም ላይ ውሏል። የምልከታ ቅጹ ጌጅ (1963) በንባብ ትምህርት ወቅት ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ የታሰቡ ዝርዝር ነጥቦችን ያካተተ ነው ብለው የተጠቀሙበት ሲሆን የምልከታ ቅጹን ወደ አማርኛ ቋንቋ በመተርጎምና በአማካሪ መምህሩ አስተያየት በማሰጠት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። በዚህም የምልከታ ቅጹን በመጠቀም በእያንዳንዱ ተጠኚ መምህር ሶስት ሶስት ጊዜ የክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ምልከታ ተካሂዷል።

### 3.3.3. ቃለ መጠይቅ

በጥናቱ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብን ለመግለጽ ይረዳ ዘንድ ለአንድ ሴት እና ለሁለት ወንድ መምህራን ቃለ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ ውሏል። ይሄውም በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ትምህርትን ለማስተማር ያላቸውን የስልጠና ሁኔታ፣ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ትግበራ፣ በአንብቦ መረዳት ትምህርት ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን እና በአንብቦ መረዳት ውጤትና ጾታ ተዛምዶ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ በሚመለከት ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸዋል።

### 3.3.4. የጥናቱ አካሄድ

ጥናቱ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለመመርመር መረጃዎች በአንብቦ መረዳት ፈተና ተሰብስበዋል።

ጥናቱ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመገምገም ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች

በአጥኚው ተዘጋጅቶ ሁለት በአማርኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪ ባላቸው መምህራን ተገምግመው እንዲሁም በአማካሪ መምህሩ አስተያየት ተሰጥቶባቸው ተማሪዎቹ እንዲፈተኗቸው ተደርጓል።

በዚህም ጥያቄዎቹ ለፈተና በቀረቡት ሁለት ምንባቦች ላይ ብቻ ተመስርተው የተዘጋጁ የምንባቡን አጠቃላይ ሃሳብ፣ ዝርዝር ሃሳቦች፣ የተፈለገ ውስን መልዕክትን ለይቶ ማውጣትን፣ የቃላት አውዳዊ ፍችን፣ የቃላት ቀጥተኛ ፍችን፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን እና ምሳሌያዊ አባባሎችን መልዕክትን መረዳትን እንዲያጠቃልሉ ተደርጓል።

የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት የተመረጠው ምንባብ ተማሪዎችን ለማንበብ የሚያነሳሳና ከዚህ በፊት አንብበውት የማያውቁት አዲስ ይዘት ያለው እንዲሆን ጥረት ተደርጓል። በዚህም የመጀመሪያው ምንባብ ከደራሲ በዓሉ ግርማ “ሀዲስ” መጽሀፍ

ከተወሰደ የልቦለድ ስራ ምንባብ፤ እንዲሁም ሁለተኛው ምንባብ ከአዲስ አድማስ ጋዜጣ የካቲት 10/2008 ዓ.ም እትም **"የኖቤል ተሸላሚዋ ኢትዮጵያዊት"** በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሁፍ ተሻሽሎ ቀርቦላቸዋል፡፡ በዚህም ተማሪዎቹ ከቀረቡላቸው ሁለት ምንባቦች ከእያንዳንዱ ምንባብ የወጡ 25 ጥያቄዎችን በድምሩ 50 ጥያቄዎች እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ አጥኚው የአንብቦ መረዳት ፈተናውን አስተማማኝነት ለመጠበቅም ፈተናው በአቅራቢያ በሚገኝ አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና ሁለት መንደር ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ህዳር 19 ቀን 2015 ዓ.ም ፈተናውን እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡ የአንብቦ መረዳት ፈተናው ውጤት አስተማማኝነትም በእኩል ክፋይ ቀመር ተሰልቶ ውጤቱ 0.710 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በዚህም የተመዘገበው ውጤት ምንም እንኳ ተቀባይነት ቢኖረውም በፈተና ጥያቄዎቹ ላይ የተስተዋሉ የፊደል፣ የስርዓተ ነጥብና ሰዋስው ስህተቶች ማስተካከያ ተደርገውበት ለዋናው ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ መረጃውም ለተማሪዎች ግልጽ ማብራሪያ ተሰጥቶ በሶስት አማርኛ መምህራን አማካኝነት በየክፍሎቻቸው እንዲፈተኑ ተደርጓል ***(አባሪ "ሀ"ን ይመልከቱ)***፡፡

በጥናቱ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብን ለመግለጽ ይረዳ ዘንድ የክፍል ውስጥ ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ይሄውም በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ትምህርትን ለማስተማር የቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜ እና የድህረ ንባብ ትምህርት አቀራረብን በሚመለከት የተዘጋጀ የምልከታ ቅጽ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የምልከታ ቅጹ ጌጅ (1963) በንባብ ትምህርት ወቅት ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ የታሰቡ ዝርዝር ነጥቦችን ያካተተ ነው ብለው የተጠቀሙበት ሲሆን የምልከታ ቅጹን ወደ አማርኛ ቋንቋ በመተርጎምና በአማካሪ መምህሩ አስተያየት በማሰጠት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በዚህም የምልከታ ቅጹን በመጠቀም በእያንዳንዱ ተጠኚ ካሉት አራት መምህራን መካከል ሶስቱ ለመጠይቁ ተሳታፊ ሲሆኑ በእያንዳንዳቸው ሶስት ሶስት ጊዜ የክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ምልከታ ተካሂዷል፡፡

በተጨማሪም በጥናቱ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብን ለመግለጽ ይረዳ ዘንድ ቃለ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ይሄውም በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ትምህርትን ለማስተማር ያላቸውን የስልጠና ሁኔታ፣ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ትግበራ፣ በአንብቦ መረዳት ትምህርት ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን እና በአንብቦ መረዳት ውጤትና ጾታ ተዛምዶ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ

በሚመለከት የካቲት 27/2015 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸዋል፡፡ መረጃዎቹም ተሰብስበዋል፡፡

### 3.3.5. የመረጃ አተናተን

በጥናቱ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ውጤትን ለመመርመር በአንብቦ መረዳት ፈተና የሚሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን SPSS 20 ስታቲስቲክስ ሶፍት ዌር አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ በዚህም የጥናቱን የመጀመሪያ መሰረታዊ ጥያቄ (የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው?) ለመመለስ በአንብቦ መረዳት ፈተና የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭ ስታትስቲክስ (አማካይ፣ ድግግሞሽ፣ መቶኛ እና የልይይት መጠንን) በመጠቀም ተሰልቷል፡፡

የጥናቱን ሁለተኛ መሰረታዊ ጥያቄ (የአንብቦ መረዳት ውጤታቸው ከጾታቸው ጋር ይዛመድ ይሆን?) ለመመለስ በአንብቦ መረዳት ፈተና የተሰበሰቡት መረጃዎች SPSS 20 ስታቲስቲክስ ሶፍት ዌር በመጠቀም መረጃዎች ከጾታ አንጻር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Sample t-test) ተሰልቷል፡፡ የጥናቱን ሶስተኛ መሰረታዊ ጥያቄ (በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ) ለመመለስም በክፍል ውስጥ የተስተዋሉ አቀራረቦችና በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በገለጻ ስልት ቀርበዋል፡፡ በመጨረሻም የተገኙ መረጃዎች በገለጻ ስልት ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት፡ የመረጃ ትንተና

## 4.1. በፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የጥናቱ ዋና ዓላማ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂል ደረጃን መመርመር ነው፡፡ በዚህም ጥናቱ በፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋነቋ አንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው? የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከተማሪዎች ጾታ ጋር ዝምድና አለውን? እንዲሁም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የመምህራን የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ምን ይመስላል? የሚሉ ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎችም ነበሩት፡፡

በቅድሚያ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው? የሚለውን የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ የተጠኚ ተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት ሁለት የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች ቀርበውላቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ምንባብ ከደራሲ በዓሉ ግርማ **"ሀዲስ"** መጽሀፍ ከተወሰደ የልቦለድ ስራ ምንባብ፤ እንዲሁም ሁለተኛው ምንባብ ከአዲስ አድማስ ጋዜጣ የካቲት 10/2008 ዓ.ም እትም **"የኖቤል ተሸላሚዋ ኢትዮጵያዊት"** በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሁፍ ተሻሽሎ ቀርቦላቸዋል፡፡ በዚህም ተማሪዎቹ ከቀረቡላቸው ሁለት ምንባቦች ከእያንዳንዱ ምንባብ የወጡ 25 ጥያቄዎችን በድምሩ 50 ጥያቄዎች ተፈትነዋል፡፡ የተመዘገቡ ውጤቶችም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 4.1፣ በሰንጠረዥ 4.2 እና በሰንጠረዥ 4.3 ተጠናቅረው ቀርበዋል፡፡

### ሀ. የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ከፈተና አንድ አንጻር

በጥናቱ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው? የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ የተጠኚ ተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት ከደራሲ በዓሉ ግርማ **"ሀዲስ"** መጽሀፍ ከተወሰደ የልቦለድ ስራ ምንባብ የተውጣጡ 25 ጥያቄዎችን ተፈትነዋል፡፡ የተመዘገቡ ውጤቶችም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 4.1 ተጠናቅሮ ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.1 የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ውጤት (ደረጃ) ከፈተና አንድ አንጻር በድግግሞሽ መጠንና በመቶኛ**

| የተመዘገበ ውጤት ከ25 | የተመዘገበ ውጤት ከ100 ሲሰላ | የድግግሞሽ መጠን | በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 7 | 28 | 3 | 1.5 |
| 8 | 32 | 7 | 3.6 |
| 9 | 36 | 9 | 4.6 |
| 10 | 40 | 17 | 8.8 |
| 11 | 44 | 13 | 6.7 |
| 12 | 48 | 8 | 4.1 |
| 13 | 52 | 30 | 15.5 |
| 14 | 56 | 31 | 16.0 |
| 15 | 60 | 16 | 8.2 |
| 16 | 64 | 15 | 7.7 |
| 17 | 68 | 9 | 4.6 |
| 18 | 72 | 6 | 3.1 |
| 19 | 76 | 10 | 5.2 |
| 20 | 80 | 7 | 3.6 |
| 21 | 84 | 3 | 1.5 |
| 22 | 88 | 4 | 2.1 |
| 23 | 92 | 4 | 2.1 |
| 24 | 96 | 2 | 1.0 |
| *አጠቃላይ ድምር* | | 194 | 100.0 |

ሰንጠረዥ 4.1 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል የፈተና አንድ ውጤትን ያሳያል፡፡ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው በጥናቱ ከተሳተፉ 194 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል 36 (18.60%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ (ከ40% በታች)፣ 21 (10.82%) ተማሪዎች ዝቅተኛ (41-50%)፣ 101 (52.06%) ተማሪዎች መካከለኛ (51-69%)፣ 23 (11.86%) ተማሪዎች በቂ (70-80%) እንዲሁም ቀሪዎቹ 13 (6.70%) ተማሪዎች ከፍተኛ (ከ81 በላይ%) አንብቦ የመረዳት ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ይህም ከአጠቃላይ ቁጥሩ ውስጥ በመጀመሪያው ፈተና 57 (29.38 ከመቶዎቹ) ተማሪዎች 12 እና ከዚያ በታች ነጥብ ያመጡ ተማሪዎች ከ50 ከመቶ በታች /ዝቅተኛ/) ያስመዘገቡ ሲሆን 137 ተማሪዎች (70.62 ከመቶዎቹ) 13 እና ከዚያ በላይ ነጥብ ያመጡ (ከ50 ከመቶ በላይ) ማስመዝገባቸውን ያመለክታል፡፡

**ለ. የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ከፈተና ሁለት አንጻር**

በጥናቱ የተጠኚ ተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት ሁለተኛ ፈተና ከአዲስ አድማስ ጋዜጣ የካቲት 10/2008 ዓ.ም እትም **"የኖቤል ተሸላሚዋ ኢትዮጵያዊት"**

በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሁፍ የተውጣጡ 25 ጥያቄዎችን ተፈትነዋል፡፡ በፈተና የተሰበሰበው መረጃም SPSS 20 ስታቲስቲክስ ሶፍት ዌርን በመጠቀም በድግግሞሽ መጠንና በመቶኛ (Frequency, and Percentage) ተሰልቷል፡፡ የተመዘገቡ ውጤቶችም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 4.2 ተጠናቅሮ ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.2 የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ውጤት (ደረጃ) ከፈተና ሁለት አንጻር በድግግሞሽ መጠንና በመቶኛ**

| የተመዘገበ ውጤት ከ25 | የተመዘገበ ውጤት ከ100 ሲሰላ | የድግግሞሽ መጠን | በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 9 | 36 | 6 | 3.1 |
| 10 | 40 | 9 | 4.6 |
| 11 | 44 | 24 | 12.4 |
| 12 | 48 | 20 | 10.3 |
| 13 | 52 | 18 | 9.3 |
| 14 | 56 | 19 | 9.8 |
| 15 | 60 | 23 | 11.9 |
| 16 | 64 | 19 | 9.8 |
| 17 | 68 | 20 | 10.3 |
| 18 | 72 | 11 | 5.7 |
| 19 | 76 | 9 | 4.6 |
| 20 | 80 | 2 | 1.0 |
| 21 | 84 | 5 | 2.6 |
| 22 | 88 | 4 | 2.1 |
| 23 | 92 | 5 | 2.6 |
| **አጠቃላይ ድምር** | | 194 | 100.0 |

ሠንጠረዥ 4.2 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል የፈተና ሁለት ውጤትን ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ እንደተመለከተው በጥናቱ ከተሳተፉ 194 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል 15 (7.73%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ (ከ40% በታች)፣ 44 (22.68%) ተማሪዎች ዝቅተኛ (41-50%)፣ 99 (51.03%) ተማሪዎች መካከለኛ (51-69%)፣ 22 (11.34%) ተማሪዎች በቂ (70-80%) እንዲሁም ቀሪዎቹ 14 (7.22%) ተማሪዎች ከፍተኛ (ከ81 በላይ%) በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ይህም ከአጠቃላይ ቁጥሩ ውስጥ በሁለተኛው ፈተና 59 (30.41 ከመቶዎቹ) ተማሪዎች 12 እና ከዚያ ነጥብ በታች (ከ50 ከመቶ በታች /ዝቅተኛ/) ያስመዘገቡ ሲሆን 135 (69.59 ከመቶዎቹ) ተማሪዎች 13 እና ከዚያ ነጥብ በላይ (ከ50 ከመቶ በላይ) ማስመዝገባቸውን ያመለክታል፡፡

### መ. የተጠኚ ተማሪዎች አጠቃላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ

በጥናቱ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው? የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ የተጠኚ ተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት የቀረቡ ሁለት ፈተናዎች ተደምረው ከ 50 ተመዝግበዋል። ድምር መረጃውም SPSS 20 ስታቲስቲክስ ሶፍት ዌርን በመጠቀም በድግግሞሽ መጠንና በመቶኛ (Frequency, and Percentage) ተሰልቷል። የተመዘገቡ ውጤቶችም በሰንጠረዥ 4.3 ተጠናቅሮ ቀርቧል።

**ሠንጠረዥ 4.3 የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል አጠቃላይ ውጤት (ደረጃ) በድግግሞሽ መጠንና በመቶኛ**

| የተመዘገበ ውጤት ከ50 | የተመዘገበ ውጤት ከ100 ሲሰላ | የድግግሞሽ መጠን | በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 16 | 32 | 2 | 1.0 |
| 17 | 34 | 5 | 2.6 |
| 18 | 36 | 1 | .5 |
| 19 | 38 | 6 | 3.1 |
| 20 | 40 | 8 | 4.1 |
| 21 | 42 | 9 | 4.6 |
| 22 | 44 | 9 | 4.6 |
| 23 | 46 | 12 | 6.2 |
| 24 | 48 | 5 | 2.6 |
| 25 | 50 | 3 | 1.5 |
| 26 | 52 | 8 | 4.1 |
| 27 | 54 | 16 | 8.2 |
| 28 | 56 | 12 | 6.2 |
| 29 | 58 | 19 | 9.8 |
| 30 | 60 | 6 | 3.1 |
| 31 | 62 | 13 | 6.7 |
| 32 | 64 | 6 | 3.1 |
| 33 | 66 | 11 | 5.7 |
| 34 | 68 | 4 | 2.1 |
| 35 | 70 | 6 | 3.1 |
| 36 | 72 | 3 | 1.5 |
| 37 | 74 | 7 | 3.6 |
| 38 | 76 | 4 | 2.1 |
| 39 | 78 | 3 | 1.5 |
| 40 | 80 | 2 | 1.0 |
| 41 | 82 | 2 | 1.0 |
| 42 | 84 | 1 | .5 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 43 | 86 | 5 | 2.6 |
| 45 | 90 | 4 | 2.1 |
| 47 | 94 | 2 | 1.0 |
| ***አጠቃላይ ድምር*** | | 194 | 100.0 |

ሠንጠረዥ 4.3 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል አጠቃላይ ውጤትን ያሳያል፡፡ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው በጥናቱ ከተሳተፉ 194 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል 22 (11.34%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ (ከ40% በታች)፣ 35 (18.04%) ተማሪዎች ዝቅተኛ (41-50%)፣ 98 (50.52%) ተማሪዎች መካከለኛ (51-69%)፣ 25 (12.89%) ተማሪዎች በቂ (70-80%) እንዲሁም ቀሪዎቹ 14 (7.22%) ከፍተኛ (ከ81 በላይ%) አንብቦ የመረዳት ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ይህም ከአጠቃላይ ቁጥሩ ውስጥ በሁለቱ ፈተናዎች ድምር ውጤት 60 (30.93 ከመቶዎቹ) ተማሪዎች 25 እና ከዚያ ነጥብ በታች (ከ50 ከመቶ በታች /ዝቅተኛ/) ያስመዘገቡ ሲሆን 134 (60.07 ከመቶዎቹ) ተማሪዎች 26 እና ከዚያ ነጥብ በላይ (ከ50 ከመቶ በላይ) ማስመዝገባቸውን ያመለክታል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ጥናቱ በቅድሚያ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው? የሚለውን የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ የተጠኚ ተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት ሁለት የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች ተፈትነዋል፡፡ ውጤቱም በሰንጠረዥ 4.4 ተጠናቅሮ ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.4 የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት (One Sample t-test)**

| ተላውጦ | ብዛት | የተመዘገበ አማካይ | መደበኛ ልይይት | የሚጠበቅ ውጤት | የቲ-ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | ጉልህነት ባለሁለት ጫፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በፈተና አንድ | 194 | 14.1907 | 3.77471 | 18.75 | 52.363 | 193 | 0.000 |
| በፈተና ሁለት | 194 | 14.7113 | 3.35146 | 18.75 | 61.139 | 193 | 0.000 |
| በአጠቃላይ ውጤት | 194 | 28.9021 | 6.96741 | 37.50 | 57.777 | 193 | 0.000 |

ሠንጠረዥ 4.4 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል አጠቃላይ ውጤትን በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ያሳያል፡፡ በተገኘው ውጤት መሰረት በጥናቱ የተሳተፉ 194 ተማሪዎች በመጀመሪያው ፈተና (የሚጠበቅ ውጤት 18.75፣ የተመዘገበ አማካይ ውጤት 14.19)፤ በሁለተኛው ፈተና ደግሞ (የሚጠበቅ ውጤት 18.75፣ የተመዘገበ አማካይ ውጤት 14.71) እንዲሁም በአጠቃላይ ፈተና ውጤት (የሚጠበቅ ውጤት 37.50፣ የተመዘገበ አማካይ ውጤት 28.90) ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል በመጀመሪያው እና በሁለተኛው ፈተና እንዲሁም

በአጠቃላይ ውጤት ከሚጠበቀው ውጤት እንደሚያንስ (ዝቅተኛ መሆኑን) ያመለክታል፡፡ ይህ በአጠቃላይ ፈተና የተመዘገበው 28.90 (57.80%) ውጤት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ አንጻር ሲታይ መካከለኛ (ከ69-51%) ላይ የሚመደብ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በተጨማሪም ሰንጠረዡ እንዳመለከተው፣ በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል የመደበኛ ልይይት መጠን የፈተና አንድ $S^2$ = 3.77471፣ ሁለተኛው ፈተና $S^2$ = 3.35146 እንዲሁም በአጠቃላይ ፈተና ውጤት $S^2$ = 6.96741 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

በተመሳሳይ ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ 4.4፣ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ስታትስቲክስ ውጤት ማየት እንደሚቻለው ተጠኚ ተማሪዎች ባስመዘገቡት አጠቃላይ በአማርኛ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤትና በሚጠበቀው ውጤት መካከል ያለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ $t(193) = 57.777$, $P<0.001$ ሆኖ ስለተገኘ ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) አንሷል፡፡ ይህም የተመዘገበው በአማርኛ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው ውጤት በታች (ዝቅተኛ) ሆኖ መገኘት በስታስቲክስ ጉልህ (ተቀባይነት ያለው) መሆኑን ያመለክታል፡፡

## 4.2. የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ከጾታ አንጻር

ጥናቱ በሁለተኛ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከተማሪዎች ጾታ ጋር ዝምድና አለውን? የሚለውን የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ ተጠኚ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ከጾታ አንጻር ተለይቶ ውጤቱ ተተንትኗል፡፡ የተመዘገቡ ውጤቶችም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 4.5 ተጠናቅሮ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 4.5 የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል አጠቃላይ ውጤት ከጾታ አንጻር በድግግሞሽ መጠንና በመቶኛ

| የተመዘገበ ውጤት ከ50 | ውጤቱ ከ100 ሲሰላ | ወንድ | | ሴት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የድግግሞሽ መጠን | በመቶኛ | የድግግሞሽ መጠን | በመቶኛ |
| 16 | 32 | 2 | 1.0 | - | - |
| 17 | 34 | 1 | .5 | 4 | 2.1 |
| 18 | 36 | 1 | .5 | - | - |
| 19 | 38 | 3 | 1.5 | 3 | 1.5 |
| 20 | 40 | 3 | 1.5 | 5 | 2.6 |
| 21 | 42 | 5 | 2.6 | 4 | 2.1 |
| 22 | 44 | 4 | 2.1 | 5 | 2.6 |
| 23 | 46 | 5 | 2.6 | 7 | 3.6 |
| 24 | 48 | 3 | 1.5 | 2 | 1.0 |
| 25 | 50 | 1 | .5 | 2 | 1.0 |
| 26 | 52 | 3 | 1.5 | 5 | 2.6 |
| 27 | 54 | 5 | 2.6 | 11 | 5.7 |
| 28 | 56 | 9 | 4.6 | 3 | 1.5 |
| 29 | 58 | 7 | 3.6 | 12 | 6.2 |
| 30 | 60 | 3 | 1.5 | 3 | 1.5 |
| 31 | 62 | 7 | 3.6 | 6 | 3.1 |
| 32 | 64 | 3 | 1.5 | 3 | 1.5 |
| 33 | 66 | 3 | 1.5 | 8 | 4.1 |
| 34 | 68 | 3 | 1.5 | 1 | .5 |
| 35 | 70 | 5 | 2.6 | 1 | .5 |
| 36 | 72 | 1 | .5 | 2 | 1.0 |
| 37 | 74 | 4 | 2.1 | 3 | 1.5 |
| 38 | 76 | 3 | 1.5 | 1 | .5 |
| 39 | 78 | 2 | 1.0 | 1 | .5 |
| 40 | 80 | 2 | 1.0 | - | - |
| 41 | 82 | - | - | 2 | 1.0 |
| 42 | 84 | 1 | .5 | - | - |
| 43 | 86 | 5 | 2.6 | - | - |
| 45 | 90 | 4 | 2.1 | - | - |
| 47 | 94 | 1 | .5 | 1 | .5 |
| Total | | 99 | 51.0 | 95 | 49.0 |

ሠንጠረዥ 4.5 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል አጠቃላይ ውጤት ከጾታ አንጻር ያሳያል፡፡ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው በጥናቱ ከተሳተፉ 99 ወንድ እና 95 ሴት በድምሩ 194 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል (ወንድ 10፣ ሴት 12) በጣም

ዝቅተኛ (ከ40% በታች)፣ (ወንድ 18፣ ሴት 16) ዝቅተኛ (41-50%)፣ (ወንድ 43፣ ሴት 52) መካከለኛ (51-69%)፣ (ወንድ 17፣ ሴት 8) በቂ (70-80%) እንዲሁም ቀሪዎቹ (ወንድ 11፣ ሴት 3) ከፍተኛ (ከ81 በላይ%) አንብቦ የመረዳት ውጤት አስመዝግበዋል። ይህም ከአጠቃላይ ቁጥሩ ውስጥ በአንብቦ መረዳት ፈተናው 28 (28.3 ከመቶዎቹ) ወንድ እና 32 (33.7 ከመቶዎቹ) ሴት ተማሪዎች 25 እና ከዚያ ነጥብ በታች (ከ50 ከመቶ በታች) ያስመዘገቡ ሲሆን 71 (71.7 ከመቶዎቹ) ወንድ እና 63 (66.3 ከመቶዎቹ) ሴት ተማሪዎች 26 እና ከዚያ ነጥብ በላይ (ከ50 ከመቶ በላይ) ማስመዝገባቸውን ያመለክታል። ይህም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎቹ በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ከወንዶች ይልቅ በርካታ ሴቶች በጣም ዝቅተኛ፣ ዝቅተኛ እና በቂ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ያረጋግጣል።

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ጥናቱ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከተማሪዎች ጾታ ጋር ዝምድና አለውን? የሚለውን የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ ተጠኚ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ከጾታ አንጻር ተለይቶ ውጤቱ ተተንትኗል። በአንብቦ መረዳት ፈተናዎቹ የተሰበሰቡ መረጃዎች SPSS 20 ስታቲስቲክስ ሶፍት ዌርን በመጠቀም በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Sample t-test) ተሰልቷል። ውጤቱም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 4..6 ተጠናቅሮ ቀርቧል።

**ሠንጠረዥ 4.6 የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ከጾታ አንጻር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Sample t-test)**

| ተላውጦ | ጾታ | ብዛት | የተመዘገበ አማካይ | መደበኛ ልይይት | የሚጠበቅ ውጤት | የቲ-ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | ጉልህነት በበለሁለት ጫፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፈተና አንድ | ወንድ | 99 | 14.7677 | 4.17922 | 18.75 | 2.195 | 98 | 0.029 |
| | ሴት | 95 | 13.5895 | 3.21398 | 18.75 | 2.206 | 94 | 0.029 |
| ፈተና ሁለት | ወንድ | 99 | 15.2929 | 3.63726 | 18.75 | 2.501 | 98 | 0.013 |
| | ሴት | 95 | 14.1053 | 2.92267 | 18.75 | 2.512 | 94 | 0.013 |
| አጠቃላይ ውጤት | ወንድ | 99 | 30.0606 | 7.64362 | 37.50 | 2.393 | 98 | 0.018 |
| | ሴት | 95 | 27.6947 | 5.98948 | 37.50 | 2.405 | 94 | 0.017 |

ሠንጠረዥ 4.6 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ከጾታ አንጻር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Sample t-test) ውጤትን ያሳያል። በሰንጠረዡ እንደተመለከተው በጥናቱ የተሳተፉ 99 ወንድ እና 95 ሴት በድምሩ 194 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ (ወንድ 14.7677 እና ሴት 13.5895) አማካይ ውጤት አስመዝግበዋል። በአንብቦ መረዳት ፈተና ሁለት ደግሞ (ወንድ 15.2929 እና ሴት 14.1053) አማካይ ውጤት አስመዝግበዋል። በተመሳሳይ በአጠቃላይ አንብቦ መረዳት ፈተና (ወንድ 30.0606 እና ሴት 27.6947) አማካይ ውጤት አስመዝግበዋል። የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ችግር በሁለቱም ጾታዎች ተማሪዎች ዘንድ

በስፋት እንደሚስተዋልና በአንጻራዊነት ከሴቶች ይልቅ ወንዶች የተሻለ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ያረጋግጣል፡፡

በተመሳሳይ ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ 4..6፤ የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Sample t-test) ስታትስቲክስ ውጤት ማየት እንደሚቻለው ተጠኚ ተማሪዎች ባስመዘገቡት አጠቃላይ በአማርኛ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤትና በሚጠበቀው ውጤት መካከል ያለው የልዩነት ጉልህነት ደረጃ የወንድ ተማሪዎች t(98) = 2.393 *P*<0.018 እንዲሁም የሴት ተማሪዎች t(94) = 2.405 *P*<0.017 ሆኖ ስለተገኘ ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) አንሷል፡፡ ይህም በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በወንዶችም በሴቶችም ተማሪዎች የተመዘገበው አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው ውጤት በታች (ዝቅ ብሎ) ሆኖ መገኘትና ከሴቶች ይልቅ ወንዶች የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸው በስታስቲክስ ጉልህ (ተቀባይነት ያለው) መሆኑን ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት የመረጃ ትንተናዎች መረዳት እንደሚቻለው፣ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ደረጃ ከሚጠበቀው በታች (ዝቅተኛ) ነው፡፡ በተጨማሪም ከሴቶች ይልቅ ወንዶች የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡

## 4.3. በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ለዚህ ጥናት አጋዥ መረጃዎች ከሆኑት መካከል አንዱ ምልከታ ነው፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ በናሙናነት በተመረጠው ትምህርት ቤት በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የንባብ ትምህርት እንዴት እየተተገበረ እንደሆነ ምልከታ ተካሂዷል፡፡ የንባብ ትምህርት አተገባበርን በክፍል ውስጥ ተገኝቶ መመልከት ያስፈለገው የንባብ ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ለማጎልበት የሚኖረውን አስተዋጾ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በዚህ መሰረት ምልከታው በእያንዳንዱ ተጠኚ ሶስት መምህራን ሶስት ሶስት ጊዜ በመግባት አንድ ምንባብ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ተከናውኗል፡፡ ተፈላጊውን የንባብ ትምህርት መረጃዎች ለማሰባሰብ የሚያግዝ የምልከታ ቅጽ የቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ ተግባራትን በአካተተ መልኩ ተዘጋጅቶ በጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በምልከታው አማካይነት በክፍል ውስጥ የሚካሄደውን የንባብ ትምህርት በተመለከተ የተገኘው መረጃም የቅድመ ንባብ ተግባራት በሰንጠረዥ 4.7፣ የንባብ ጊዜ ተግባራት በሰንጠረዥ 4.8 እና የድህረ ንባብ ተግባራት በሰንጠረዥ 4.9 እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 4.7 የቅድመ ንባብ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ በምልከታ የተሰበሰበ መረጃ

| ተ.ቁ | ተግባራት | ምልከታ አንድ | | ምልከታ ሁለት | | ምልከታ ሶስት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ተከናውኗል | አልተከናወነም | ተከናውኗል | አልተከናወነም | ተከናውኗል | አልተከናወነም |
| 1.1 | ተማሪዎች የሚያነቡበትን ምክንያት አስተዋውቀዋል | 3 | - | 3 | - | 2 | 1 |
| 1.2 | ተማሪዎች የአንባቦ መረዳት ፍላጎት እንዲያድርባቸዉ አድርገዋል፣ | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 |
| 1.3 | ተማሪዎች የቀደመ ዕዉቀታቸዉን አሁን ከሚማሩት ንባብ ጋር እንዲያያዩዘት አነቃቅተዋል | 2 | 1 | 2 | 1 | 3 | - |
| 1.4 | የዕለቱን የአንብቦ መረዳት ትምህርት ርዕስ አስተዋዉቀዋል | 3 | - | 3 | - | 3 | - |
| 1.5 | በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል አድርገዋል፣ | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 |
| 1.6 | ተማሪዎች እንዲወያዩ አድረገዋል፣ | 2 | 1 | 3 | - | 2 | 1 |
| 1.7 | ለቁልፍ ቃላት ፍቺ ሰጥተዋል፣ | 1 | 2 | 3 | - | 3 | - |

ከሰንጠረዥ 4.7 መመልከት እንደሚቻለው በናሙናነት የተመረጡ መምህራን ሶስት ጊዜ ያህል የክፍል ውስጥ ምልከታ ተካሂዷል፡፡ በዚህም በቅድመ ንባብ ትምህርት በመጀመሪያውና በሁለተኛው ምልከታ ሶስቱም መምህራን ተማሪዎች የሚያነቡበትን ምክንያት አስተዋውቀዋል፡፡ በተቃራኒው በሶስተኛው ምልከታ ሁለቱ መምህራን ተማሪዎች የሚያነቡበትን ምክንያት ያስተዋወቁ ሲሆን ቀሪው አንድ መምህር አላስተዋወቀም፡፡ ይህም አማርኛ ቋንቋ መምህራኑ በቅድመ ንባብ ትምህርት ደረጃ ተማሪዎች የሚያነቡበትን ምክንያት ከማስተዋወቅ አንጻር ጠንካራ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡

በተጨማሪም በቅድመ ንባብ ትምህርት ሂደት ሁለቱ መምህራን ተማሪዎች የአንባቦ መረዳት ፍላጎት እንዲያድርባቸዉ ያላደረጉ ሲሆን ቀሪው አንድ መምህር በተቃራኒው ተማሪዎች የአንባቦ መረዳት ፍላጎት እንዲያድርባቸዉ አድርገዋል፡፡ ይህም በቅድመ ንባብ ትምህርት ደረጃ አብዛኞቹ መምህራን ተማሪዎች የአንባቦ መረዳት ፍላጎት እንዲያድርባቸዉ ከማነቃቃት አንጻር ድክመት እንዳለባቸው ያመለክታል፡፡

ከሰንጠረዥ 4.7 ተራ ቁጥር 3 መመልከት እንደሚቻለው በቅድመ ንባብ ትምህርት በመጀመሪያውና በሁለተኛው ምልከታ ሁለት መምህራን ተማሪዎች የቀደመ ዕዉቀታቸዉን አሁን ከሚማሩት ንባብ ጋር እንዲያያዩዘት አነቃቅተዋል፡፡ በተቃራኒው

አንዱ መምህር ተማሪዎች የቀደመ ዕዉቀታቸዉን አሁን ከሚማሩት ንባብ ጋር እንዲያያዩዙት አላነቃቁም፡፡ በሶስተኛው ምልከታ ደግሞ ሶስቱም መምህራን ተማሪዎች

የቀደመ ዕዉቀታቸዉን አሁን ከሚማሩት ንባብ ጋር እንዲያያዩዙት አነቃቅተዋል፡፡ ይህም በቅድመ ንባብ ትምህርት ደረጃ አብዛኞቹ መምህራን ተማሪዎች የቀደመ ዕዉቀታቸዉን አሁን ከሚማሩት ንባብ ጋር እንዲያያዩዘት በማድረግ የንባ ትምህርቱን እንደሚጀምሩ ያመለክታል፡፡

በተጨማሪም በቅድ መንባብ ትምህርት ሂደት በሶስቱም ምልከታዎች ሶስቱም መምህራን የዕለቱን የአንብቦ መረዳት ትምህርት ርዕስ አስተዋዉቀዋል፡፡ ይህም በቅድመ ንባብ ትምህርት ደረጃ ሁሉም መምህራን የዕለቱን የአንብቦ መረዳት ትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅ እንደሚጀምሩ ያመለክታል፡፡

ከሰንጠረዥ 4.7 ተራ ቁጥር 5 መመልከት እንደሚቻለው በቅድመ ንባብ ትምህርት በመጀመሪያውና በሁለተኛው ምልከታ ሁለት መምህራን በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል ገለጻ አላደረጉም፡፡ በተቃራኒው አንዱ መምህር ገለጻ አድርገዋል፡፡ በተቃራኒው በሶስተኛው ምልከታ ሁለቱ መምህራን በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል ገለጻ ያደረጉ ሲሆን ቀሪው አንድ መምህር ገለጻ አላደረጉም፡፡ ይህም በቅድመ ንባብ ትምህርት ደረጃ አብዛኞቹ መምህራን ለተማሪዎች በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል በመግለጽ (በመጠየቅ) የንባብ ትምህርቱን እንደሚጀምሩ ያመለክታል፡፡

ከሰንጠረዥ 4.7 ተራ ቁጥር 6 መመልከት እንደሚቻለው በቅድመ ንባብ ትምህርት በመጀመሪያውና በሶስተኛው ምልከታ ሁለት መምህራን ተማሪዎች እንዲወያዩ ያደረጉ ሲሆን ቀሪው አንድ መምህር በተቃራኒው ተማሪዎችን አላወያዩም፡፡ በተቃራኒው በሶስተኛው ምልከታ ወቅት ሶስቱም መምህራን ተማሪዎች እንዲወያዩ አድረገዋል፡፡ ይህም በቅድመ ንባብ ትምህርት ደረጃ አብዛኞቹ መምህራን ተማሪዎች እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን እንደሚጀምሩ ያመለክታል፡፡

ከሰንጠረዥ 4.7 ተራ ቁጥር 7 መመልከት እንደሚቻለው በቅድመንባብ ትምህርት በሁለተኛውና በሶስተኛው ምልከታ ሶስቱም መምህራን ለቁልፍ ቃላት ፍቺ ሰጥተዋል፡፡ በተመሳሳይ በመጀመሪያው ምልከታ አንዱ መምህር ለቁልፍ ቃላት ፍቺ የሰጠ ሲሆን ቀሪዎቹ ሁለት መምህራን ለቁልፍ ቃላት ፍቺ አልሰጡም፡፡ ይህም በቅድመ ንባብ ትምህርት ደረጃ አብዛኞቹ መምህራን ለተማሪዎች ለቁልፍ ቃላት ፍቺ በመስጠት የንባብ ትምህርቱን እንደሚጀምሩ ያመለክታል፡

ሠንጠረዥ 4.8 በምልከታ የንባብ ጊዜ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ የተሰበሰበ መረጃ

| ተ.ቁ | ተግባራት | ምልከታ አንድ | | ምልከታ ሁለት | | ምልከታ ሶስት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ተከናውኗል | አልተከናወነም | ተከናውኗል | አልተከናወነም | ተከናውኗል | አልተከናወነም |
| 2.1 | ጥያቄዎችን በመስጠት አንብቦ መረዳት ክሂል እንዲከናወን አድርገዋል፣ | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 |
| 2.2 | ለንባቡ ጊዜ ወስነዉ (ደቂቃ) ሰጥተዋል፣ | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 |
| 2.3 | ለተጠየቁት ጥያቄ ምጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል፣ | 1 | 2 | 3 | - | 3 | - |
| 2.4 | ስዕልን (ምስልን) በማንበብ ወይም ቅፅ በመሙላት መልመጃዎችን እንዲሰሩ አድረገዋል፣ | - | 3 | - | 3 | 1 | 2 |
| 2.5 | ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ አድርገዋል፣ | - | 3 | 2 | 1 | 1 | 2 |
| 2.6 | የቃላት ፍቺ ከአዉድ አንፃር እንዲገምቱ አድርገዋል፣ | 3 | - | 3 | - | - | 3 |

ከሠንጠረዥ 4.8 መመልከት እንደሚቻለው በናሙናነት የተመረጡ መምህራን ሶስት ጊዜ ያህል የክፍል ውስጥ ምልከታ ተካሂዷል፡፡ በዚህም በንባብ ጊዜ ትምህርት በመጀመሪያውና በሁለተኛው ምልከታዎች አንዱ መምህር ጥያቄዎችን በመስጠት አንብቦ መረዳት ክሂል እንዲከናወን ያደረገ ሲሆን በተቃራኒው ሁለቱ መምህራን ጥያቄዎችን በመስጠት አንብቦ መረዳት ክሂል እንዲከናወን አላደረጉም፡፡ በሶተኛው ምልከታ ደግሞ ሁለቱ መምህራን ጥያቄዎችን በመስጠት አንብቦ መረዳት ክሂል እንዲከናወን ያደረጉ ሲሆን አንዱ መምህር አላደረገም፡፡ ይህም አብዛኞቹ መምህራን በንባብ ጊዜ ትምህርት ጥቄዎችን በመስጠት አንብቦ መረዳት ክሂል ትምህርት እንዲከናወን ከማድረግ አንጻር ደካማ እንደሆኑ ያመለክታል፡፡

ከሰንጠረዥ 4.8 ተራ ቁጥር 2 መመልከት እንደሚቻለው በምንባብ ጊዜ ትምህርት በመጀመሪያው ምልከታ ሁለት መምህራን ለንባቡ ጊዜ ወስነዉ (ደቂቃ) ያልሰጡ ሲሆን አንዱ መምህር ግን የንባብ ጊዜውን ወስኖ ሰጥቷል፡፡ በተቃራኒው በሁለተኛውና በሶስተኛው ምልከታ ወቅት ሁለት መምህራን ለንባቡ ጊዜ ወስነዉ (ደቂቃ) የሰጡ ሲሆን ቀሪው አንድ መምህር የንባ ጊዜ አልሰጠም፡፡ ይህም አብዛኞቹ መምህራን በምንባብ ጊዜ ትምህርት ለንባቡ ጊዜ (ደቂቃ) ወስነዉ በመስጠት አንብቦ መረዳት ክሂልን እንደሚያስተምሩ ያመለክታል፡፡

ከሰንጠረዥ 4.8 ተራ ቁጥር 3 መመልከት እንደሚቻለው በንባብ ጊዜ ትምህርት በመጀመሪያው ምልከታ ሁለት መምህራን ለተጠየቁት ጥያቄ ምጋቤ ምላሽ ያልሰጡ ሲሆን አንዱ መምህር ግን ሰጥቷል፡፡ በተቃራኒው በሁለተኛውና በሶስተኛው ምልከታ ወቅት ሶስቱም መምህራን ለጠየቁት ጥያቄ ምጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም አብዛኞቹ መምህራን በንባብ ጊዜ ትምህርት ለተጠየቁት ጥያቄ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት እንደሚያስተምሩ ያመለክታል፡፡

ከሰንጠረዥ 4.8 ተራ ቁጥር 4 መመልከት እንደሚቻለው በንባብ ጊዜ ትምህርት በመጀመሪያውና በሁለተኛው ምልከታ ሶስቱም መምህራን ስዕልን ወይም ምስልን በማንበብ ወይም ቅፅ በመሙላት መልመጃዎችን እንዲሰሩ ያላደረጉ ሲሆን በሶስተኛው ምልከታ ወቅት በተቃራኒው አንድ መምህር ብቻ ስዕልን ወይም ምስልን በማንበብ ወይም ቅፅ በመሙላት መልመጃዎችን እንዲሰሩ አድርገዋል፡፡ ይህም አብዛኞቹ መምህራን በንባብ ጊዜ ትምህርት ተማሪዎች ስዕልን ወይም ምስልን በማንበብ ወይም ቅፅ በመሙላት መልመጃዎችን እንዲሰሩ ከማድረግ አኳያ ድክመት እንደሚታይባቸው ያመለክታል፡፡

ከሰንጠረዥ 4.8 ተራ ቁጥር 5 መመልከት እንደሚቻለው በንባብ ጊዜ ትምህርት በመጀመሪያው ምልከታ ሶስቱም መምህራን ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ አላደረጉም፡፡ በሁለተኛው ምልከታ ደግሞ ሁለት መምህራን ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ ያደረጉ ሲሆን አንዱ መምህር አላደረገም፡፡ በተቃራኒው በሶተኛው ምልከታ አንዱ መምህር ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ ያደረገ ሲሆን ቀሪዎቹ ሁለት መምህራን ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ አላደረጉም፡፡ ይህም አብዛኞቹ መምህራን በንባብ ጊዜ ትምህርት ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ በማድረግ ከማስተማር አኳያ ድክመት እንደሚታይባቸው ያመለክታል፡፡

ከሰንጠረዥ 4.8 ተራ ቁጥር 6 መመልከት እንደሚቻለው በንባብ ጊዜ ትምህርት በሶስቱም ምልከታዎች ሶስቱም መምህራን የቃላትን ፍቺ ከአዉድ አንፃር እንዲገምቱ አድርገዋል፡፡ ይህም አብዛኞቹ መምህራን በንባብ ጊዜ ትምህርት የቃላትን ፍቺ ከአዉድ አንፃር እንዲገምቱ በማድረግ አንብቦ መረዳት ክሂልን እንደሚያስተምሩ ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ 4.9 በምልከታ የድህረንባብ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ የተሰበሰበ መረጃ

| ተ.ቁ | ተግባራት | ምልከታ አንድ | | ምልከታ ሁለት | | ምልከታ ሶስት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ተከናውኗል | አልተከናወነም | ተከናውኗል | አልተከናወነም | ተከናውኗል | አልተከናወነም |
| 3.1 | ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳታቸዉን መምህሩ ጥያቄ በመጠየቅ አረጋግጠዋል | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 |
| 3.2 | ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸዉ ገጠመኝ ጋር እንዲያይዙት አድርገዋል | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 |
| 3.3 | ተማሪዎች ምንባቡን እንዲገመግሙ አድርገዋል፣ | - | 3 | - | 3 | 3 | - |
| 3.4 | ከንባቡ ጋር ሌሎች ክሂሎች ጋር በማጣመር ጥያቄ አቅርበዋል | - | 3 | 2 | 1 | 1 | 2 |

ከሠንጠረዥ 4.9 መመልከት እንደሚቻለው በናሙናነት የተመረጡ መምህራን በድህረንባብ ትምህርት በሶስቱም ምልከታዎች ወቅት ሁለት ሁለት መምህራን ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳታቸዉን ጥያቄ በመጠየቅ ያረጋገጡ ሲሆን ቀሪው አንድ መምህር ግን ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳታቸዉን ጥያቄ በመጠየቅ ሲያረጋግጡ አልተስተዋለም፡፡ ይህም አብዛኞቹ መምህራን በድህረንባብ ትምህርት ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳታቸዉን ጥያቄ በመጠየቅ አንብቦ መረዳት ክሂልን እንደሚያስተምሩ ያመለክታል፡፡

ከሰንጠረዥ 4.9 ተራ ቁጥር 2 መመልከት እንደሚቻለው በድህረንባብ ትምህርት በመጀመሪያውና በሁለተኛው ምልከታ አንድ አንድ መምህር በሶስተኛው ምልከታ በበኩሉ ሁለት መምህራን ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸዉ ገጠመኝ ጋር እንዲያይዙት ያደረጉ ሲሆን በተቃራኒው በምልከታ አንድና ሁለት ሁለት መምህራን እንዲሁም በሶስተኛው ምልከታ ወቅት አንድ መምህር ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸዉ ገጠመኝ ጋር እንዲያይዙት አላደረጉም፡፡

ይህም አብዛኞቹ መምህራን በድህረንባብ ትምህርት ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸዉ ገጠመኝ ጋር እንዲያይዙት በማድረግ አንብቦ መረዳት ክሂልን እንደማያስተምሩ ያመለክታል፡፡

ከሰንጠረዥ 4.9 ተራ ቁጥር 3 መመልከት እንደሚቻለው በድህረንባብ ትምህርት በመጀመሪያውና በሁለተኛው ምልከታ ሶስቱም መምህራን ተማሪዎች ምንባቡን እንዲገመግሙ አላደረጉም ነበር፡፡ በተቃራኒው በሶስተኛው ምልከታ ሶስቱም መምህራን ተማሪዎች ምንባብ እንዲገመግሙ ማድረጋቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህም አብዛኞቹ መምህራን

በድህረንባብ ትምህርት ተማሪዎች ምንባቡን እንዲገመግሙ ተግባራትን እንደማይሰጡ ያመለክታል፡፡

ከሠንጠረዥ 4.9 ተራ ቁጥር 4 መመልከት እንደሚቻለው በድህረ ንባብ ትምህርት በመጀመሪያው ምልከታ ሶስቱም መምህራን ከንባቡ ጋር ሌሎች ክሂሎች ጋር በማጣመር ጥያቄ አላቀረቡም ነበር፡፡ በሁለተኛው ምልከታ በተቃራኒው ሁለት መምህራን የንባብ ትምህርትን ሌሎች ክሂሎች ጋር በማጣመር ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን ቀሪው አንድ መምህር ግን አላቀረበም ነበር፡፡ በሶስተኛው ምልከታ በተመሳሳይ አንድ መምህር ከንባቡ ጋር ሌሎች ክሂሎች ጋር በማጣመር ጥያቄ ያቀረበ ሲሆን ቀሪዎቹ ሁለት መምህራን ግን አላቀረቡም ነበር፡፡ ይህም አብዛኞቹ መምህራን በድህረንባብ ትምህርት የንባብ ትምህርትን ሌሎች ክሂሎች ጋር በማጣመር እንደማያስተምሩ ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማዳበር እንዲያስችል የንባብ ትምህርት በሶስት (በቅድመ ንባብ፣ በንባብ ጊዜ እና በድህረ ንባብ) ደረጃዎች ተከፍሎ መሰጠት እንዳለበት ይታመናል፡፡ ሆኖም በምልከታው ውጤት መሰረት ተጠኚ መምህራን በቅድመንባብ እና በንባብ ጊዜ ተግባራት ጠንካራ (የተሻሉ) መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን በተቃራኒው በድህረንባብ ትምህርት ተግባራት ደረጃ በጣም ደካማ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

## 4.4. የንባብ ትምህርት አተገባበርንና የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳትን በተመለከተ በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ለዚህ ጥናት የንባብ ትምህርት አተገባበርንና የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳትን በተመለከተ አጋዥ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ ከዋሉት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መካከል አንዱ ቃለመጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ በናሙናነት የተመረጡ መምህራን ጋር ቃለመጠይቅ ተካሂዷል፡፡ በዚህም በቃለመጠይቅ ወቅት በቅድሚያ መምህራኑ "በትምህርት ስልጠና ጊዜ የአንብቦ መረዳት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ በበቂ ሁኔታ ስልጠና አግኝቻለሁ ብለዉ ያምናሉ?" በማለት ተጠይቀው ነበር፡፡

በዚህም በቃለመጠይቁ ላይ የተሳተፉት አንድ ሴት እና ሁለት ወንድ (በድምሩ ሶስት መምህራን) መካከል ሁለቱ መምህር አንድ እና መምህር ሶስት "በበቂ ሁኔታ ወስደናል የሚያስብል ክህሎት ባናዳብርበትም በተለይ በዲግሪ መርሃ ግብር ከሞላ ጎደል በመጠኑ ወስደናል፡፡

ሆኖም ስልጠናዉን በወሰድንበት መጠን ትምህርቱን እየሰጠን ነው ብሎ ብሎ ደፍሮ መናገር አይቻልም፡፡ የወሰድኩትም ስልጠና ጠለቅ ያለ ስልጠና ነዉ ማለት አይቻልም" በማለት አስረድተዋል፡፡ በተቃራኒው መምህር ሁለት "በሁሉም በተማርኳቸዉ መርሃ ግብር ትምህርቶች ስልጠናዉን ወስጃለሁ የተማሪዎች አቀባበል ግን ከወሰድኩት ስልጠና ጋር ለማስኬድ በርካታ እንቅፋቶች አሉ" በማለት መልሰዋል፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነዘዴ ዙሪያ ምንም ዓይነት ስልጠና ወስጄ አላዉቅም፡፡ ይህም መምህራኑ በትምህርት ስልጠና ጊዜ

የአንብቦ መረዳት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ስልጠና ቢሰጡም መምህራን በስራ ላይ ለመተግበር እንደሚቸገሩ ያመለክታል፡፡

በቃለ መጠይቁ በሁለተኛ ደረጃ የቀረበው ጥያቄ "በስልጠና ጊዜ ያገኙትን ትምህርት ተግባር ላይ ለማዋል ችለዋል? ካልቻሉስ ችግሩ ምንድን ነዉ?" የሚል ነበር፡፡ በዚህም በቃለመጠይቁ ላይ የተሳተፉት ሶስት መምህራን በአንድ ክፍል ዉስጥ በርካታ ተማሪዎች መኖር እና የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ በቁጥር ዉስን መሆን ዋነኛ ችግሮች መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

በቃለ መጠይቁ ከተሳተፉት ሶስት መምህራን መካከል ሁለቱ ደግሞ የአየር ንብረቱ ሞቃታማ መሆን እና ለትምህርቱ የተመደበዉ የክፍለ ጊዜ መጠን ሁለት መሆኑ በስልጠና ጊዜያገኙትን ትምህርት ተግባር ላይ ለማዋል ችግር እንደፈጠረባቸው አብራርተዋል፡፡ እንዲሁም አንድ መምህር በስልጠና ጊዜያገኙትን ትምህርት ተግባር ላይ ለማዋል ከታች ክፍል ይዘዉት የመጡት የንባብ ክሂል ዕዉቀታቸዉ ዝቅተኛ መሆኑ፣ የስምንተኛ ክፍል ማለፊያ ነጥብ ዝቅተኛ መሆኑ እና ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ላይ ለመሳተፍ ፈቃደኛ አለመሆን (ፍላጎት አለመኖር) ሌሎች ተጨማሪ ችግሮች መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

በቃለ መጠይቁ በሶስተኛ ደረጃ የቀረበው ጥያቄ "የአንብቦ መረዳት ትምህርት ሲያስተምሩ አዘዉትረዉ የሚጠቀሙት የትኞቹን የንዑሳን የንባብ ክሂሎችን ነዉ?" የሚል ነበር፡፡ በዚህም በቃለመጠይቁ ላይ የተሳተፉት ሶስት መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርት ሲያስተምሩ የአሰሳ ንባብ ንዑስ ክሂልን አዘውትረው እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ እንደአስፈላጊነቱ ሁሉም ተማሪዎች በለሆሳስ ወይም በአርምሞ እንዲያነቡ ሌላ ጊዜ ደግሞ በክፍል ድምፃቸዉን ክፍ አድርገዉ እንዲያነቡ እንደሚያደርጉ አብራርተዋል፡፡

በቃለ መጠይቁ ላይ ከተሳተፉት ሶስት መምህራን መካከል ሁለቱ ከአሰሳ ንባብ በተጨማሪ በቤታቸዉ ደግሞ ሰፊ ፅሁፍ እንዲያነቡ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

ሁሉም ተማሪዎች በለሆሳስ ወይም በአርምሞ እንዲያነቡ በደቂቃ ተምኖ መስጠት ሌላዉ ደግሞ በክፍል ድምፃቸዉን ክፍ አድርገዉ እንዲያነቡ እንደሚያደርጉ አብራርተዋል፡፡

በቃለ መጠይቁ በአራተኛ ደረጃ የቀረበው ጥያቄ "የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ፍላጎት በመምህሩ ጥረትና አቀራረብ ይወሰናል ብለዉ ያምናሉ?" የሚል ነበር፡፡ በዚህም በቃለመጠይቁ ላይ የተሳተፉት ሶስት መምህራን መካከል ሁለቱ መስማማታቸውን እንደሚከተለው አስረድተዋል፡፡

"አዎ አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም እኔ ተግቼ በአበረታታኋቸዉ ቁጥር ይበረታታሉ፡፡ ችላ ባልኩ ቁጥር ደግሞ የእነሱም የአንብቦ መረዳት ክሂላቸዉ ይዳከማል ከቤታቸዉም ሆነ ከየትኛዉም ሊነበብ ከሚያስችል ነገር ሁሉ ለማንበብም መዘናጋት ሊኖር ይችላል" መምህር ሁለት፡፡ መምህር ሶስት በበኩላቸው "አዎ አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም ተማሪ መምህሩን ይመስላል፡፡

መምህሩ በየጊዘዉ የተለያዩ ጥረቶችንና ማበረታቻዎችን በተጠቀመ ቁጥር ተማሪዎችም የተሻሉ እየሆኑ የመምህሩን ሁልጊዜ መምጣት በጉጉት ይጠብቃሉ ለዚህም ተነሳሽነት የመምህሩ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ናቸዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መምህሩ ግድ የለሽ ከሆነ ተማሪዎቹም ከሱ የባሱ እየሆኑ ያድጋሉ፡፡ ስለዚህ ለተማሪዎች መሻሻልም ሆነ ዉድቀት የመምህሩ ሚና ከፍተኛ ነዉ" በማለት ገልጸዋል፡፡

እንዲሁም ቀሪው አንድ መምህር በበኩሉ የመምህሩ ጥረትና አቀራረብ እንደ አንድ ዋነኛ ግብዓት ቢሆንም ዋናዉ ግን የክፍለ ጊዜ ማነስ እና የተማሪዉ የክፍል ጥምርታ ወይም በአንድ ክፍል ዉስጥ ከ80-100 ተማሪዎች መኖር ካልተስተካከሉ የመምህሩ ፍላጎትና ጥረት ብቻዉን የተፈለገዉን ዉጤት ሊያስገኝ አይችልም በማለት አብራርቷል፡፡

በቃለ መጠይቁ በአምስተኛ ደረጃ የቀረበው ጥያቄ "የአንብቦ መረዳት ትምህርት ከተማሪዎች ፆታ ጋር ያለዉ ዝምድና ምን ይመስላል?" የሚል ነበር፡፡ በዚህም በቃለመጠይቁ ላይ የተሳተፉት ሶስት መምህራን መካከል ሁለቱ ሴቶች አንብቦ መረዳት ትምህርትን ለመማር ቢፈልጉም በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ሲጠየቁ ፍርሃትና መሸማቀቅ (ሀፍረት) እንደሚስተዋልባቸው አስረድተው በአንብቦ መረዳት ውጤታቸውም ወንድ ተማሪዎች እንደሚበልጡ ተናግረዋል፡፡ በተመሳሳይ ሶስተኛው መምህር ሴት ተማሪዎች ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ የማፈርና ተሳትፏቸዉም ዝቅ ያለ ነው በማለት መልሰዋል፡፡

ይህም በአጠቃላይ ሲታይ ሴት ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ትምህርት ውጤታቸው ከወንዶች ዝቅ ሊል እንደሚችል ያመለክታል፡፡

## 4.5. የውጤት ማብራሪያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂል ደረጃ መፈተሽ ነው፡፡ ለጥናቱ ዓላማ መሳካትም በቅድሚያ የተፈተሸው የምርምር ዓላማ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ማሳየት /መግለጽ/ ነበር፡፡ በዚህም የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታን በሚመለከት የተሰበሰቡ መረጃዎች SPSS 20 ስታቲስቲክስ ሶፍት ዌርን በመጠቀም በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት (One Sample t-test) ተሰልተዋል፡፡

በተገኘው ውጤት መሰረትም በተገኘው ውጤት መሰረት በጥናቱ የተሳተፉ 194 ተማሪዎች በመጀመሪያው ፈተና (የሚጠበቅ ውጤት 18.75፣ የተመዘገበ አማካይ ውጤት 14.19)፣ በሁለተኛው ፈተና (የሚጠበቅ ውጤት 18.75፣ የተመዘገበ አማካይ ውጤት 14.71) በአጠቃላይ ፈተና ውጤት ደግሞ (የሚጠበቅ ውጤት 37.50፣ የተመዘገበ አማካይ ውጤት 28.90) ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ እንዲሁም የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል የመደበኛ ልይይት መጠን የፈተና አንድ $S^2 = 3.77471$፣ እንዲሁም ሁለተኛው ፈተና $S^2 = 3.35146$ ሆኖ በመመዝገቡ የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል መጠን ዝቅተኛ ልዩነት እንዳለው ያመለክታል፡፡ ይህም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ

የመረዳት ክሂል የተመዘገበው አማካይ ውጤት በመጀመሪያው እና በሁለተኛው ፈተና እንዲሁም በአጠቃላይ ውጤት) ከሚጠበቀው ውጤት በታች (ዝቅተኛ) ከአንብቦ መረዳት ደረጃዎች አንጻር ሲታይም መካከለኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ባስመዘገቡት አጠቃላይ በአማርኛ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤትና በሚጠበቀው ውጤት መካከል ያለው የልዩነት ጉልህነት ደረጃ t(193) = 57.777 $P<0.001$ ሆኖ ስለተገኘ ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) አንሷል፡፡ ይህም የተመዘገበው በአማርኛ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው ውጤት በታች ሆኖ (ዝቅ ብሎ) መገኘት በስታስቲክስ ጉልህ (ተቀባይነት ያለው) መሆኑን ያመለክታል፡፡

እንደ ፒኩልስኪ እና ቻርድ፣ (2005) አገላለጽ፣ አንብቦ መረዳት ትርጉም ያለው ግንዛቤና መልዕክት ለማግኘት አንባቢው ከሚያነበው ጽሁፍ ጋር የሚያደርገው የሀሳብ ልውውጥ የማሰላሰል መስተጋብራዊ ግንኙነት ነው፡፡ የአስተሳሰብ አድማስን ስለሚያሰፋ፣ ሁለገብ ዕውቀት ስለሚያላብስና በራስ መተማመንን ስለሚያጎለብት ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል (ዳዊት፣ 2008)፡፡ ማንኛውም ሰው ማወቅ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ሊያገኝ ከሚችልባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው ንባብ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የጠለቀ ዕውቀት እንዲኖራቸውና በዚህም በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ከሚያስፈልጓቸው መሰረታዊ ክሂሎች መካከል አንዱ የአንብቦ መረዳት ክሂል ነው፡፡ በተመሳሳይም ናታል (1982) ተማሪዎች የንባብ ክሂላቸውን እያዳበሩ ሲሄዱ ያለማንም እርዳታ በተገቢው ፍጥነት ከበቂ ግንዛቤ ጋር መልዕክትን አንብበው መረዳት ይችላሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡ ጌትነት (1990) በጋሞኛ ቋንቋ አፋቸውን በፈቱ የአርባ ምንጭ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መዋቅር እውቀትና በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ጽሁፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ባካሄዱት ጥናት ውጤት መሰረትም በጋሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ አፋቸውን ከፈቱ ተማሪዎች አንጻር ሲታዩ በአማርኛ ቋንቋ መዋቅር እውቀታቸውም ሆነ በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ጽሁፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ተረጋግጧል፡፡ በተሾመ (1997) ጥናት ውጤት መሰረትም በደቡብ ኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በከምባታ ጠንባሮ ዞን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ከተማሪዎች የክፍል ደረጃ አኳያ በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ጽሁፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝና በንባብ ፍጥነታቸውም ዘገምተኛ መሆኑ ታውቋል፡፡ በተመሳሳይ የዘውዱ (1998) እና የመኮንን (2000) ጥናት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህ ጥናትም በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ተካሂዶ የተማሪዎቹ በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ደረጃ ከሚጠበቀው አማካይ በታች መሆኑን በማሳየቱ የጌትነት (1990)፣ የተሾመ (1997)፣ የዘውዱ (1998) እና የመኮንን 2000) ጥናቶች የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች

የአንብቦ መረዳት ችሎታ (ክሂል) ደረጃ ዝቅተኛ ነው ሲሉ የገለጹትን የጥናት ውጤት ትክክለኛነት አረጋግጧል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተፈተሸው የምርምር ዓላማ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከተማሪዎች ጾታ ጋር ያለውን የተዛምዶ ደረጃ መግለጽ ነበር፡፡ በዚህም የተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ መረዳት ክሂል ደረጃ ከተማሪዎች ጾታ ጋር ያለውን የተዛምዶ ደረጃ ለመግለጽ የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ክሂልን በሚመለከት በአንብቦ መረዳት ፈተናዎቹ የተሰበሰቡ መረጃዎች SPSS 20 ስታቲስቲክስ ሶፍት ዌርን በመጠቀም በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Sample t-test) ተሰልተዋል፡፡

በተገኘው ውጤት መሰረትም በጥናቱ የተሳተፉ 99 ወንድ እና 95 ሴት በድምሩ 194 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አማካይ ውጤት በአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ ወንድ ተማሪ 14.7677 እና ሴት ተማሪዎች 13.5895፣ በአንብቦ መረዳት ፈተና ሁለት ደግሞ ወንድ ተማሪዎች 15.2929 እና ሴት ተማሪዎች 14.1053 በተመሳሳይ በአጠቃላይ አንብቦ መረዳት ፈተና ወንድ ተማሪዎች 30.0606 እና ሴት ተማሪዎች 27.6947 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ችግር በሁለቱም ጾታዎች ተማሪዎች ዘንድ በስፋት እንደሚስተዋልና በአንጻራዊነት ከሴቶች ይልቅ ወንዶች የተሻለ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ያረጋግጣል፡፡

በተመሳሳይ የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Sample t-test) ስታትስቲክስ ውጤት ማየት እንደሚቻለው ተጠኚ ተማሪዎች ባስመዘገቡት አጠቃላይ በአማርኛ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤትና በሚጠበቀው ውጤት መካከል ያለው የልዩነት ጉልህነት ደረጃ የወንድ ተማሪዎች $t(98) = 2.393$ $P<0.018$ እንዲሁም የሴት ተማሪዎች $t(94) = 2.405$ $P<0.017$ ሆኖ ስለተገኘ ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) አንሷል፡፡ ይህም በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በወንዶችም በሴቶችም ተማሪዎች የተመዘገበው አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው ውጤት በታች (ዝቅ ብሎ) ሆኖ መገኘትና ከሴቶች ይልቅ ወንዶች የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸው በስታስቲክስ ጉልህ (ተቀባይነት ያለው) መሆኑን ያመለክታል፡፡

በጥናቱ በሶስተኛ ደረጃ የተፈተሸው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የመምህራን የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ምን ይመስላል? የሚል ነበር፡፡ በጥናቱ የመምህራንን የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ለመፈተሽ ጥቅም ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የክፍል ምልከታ ነው፡፡ በዚህም በምልከታ በተገኘው ውጤት መሰረት ተጠኚ መምህራን በቅድመ ንባብ እና በንባብ ጊዜ ተግባራት ላይ ጥቂት ድክመቶች (ወጣገባነት) የተስተዋሉባቸው ቢሆንም እንደ አጠቃላይ ሲታይ ጠንካራ (የተሻሉ) መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በተቃራኒው በድህረ ንባብ ትምህርት ተግባራት ደረጃ በጣም ደካማ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህ የመምህራኑ በድህረ ንባብ ትምህርት ተግባራት

ደረጃ በጣም ደካማ መሆን ካሉባቸው የቅድመ ንባብና የንባብ ጊዜ ጥቂት ተግባራት ድክመት ጋር ሲደማመር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ይጠቁማል፡፡ በጥናቱ የመምህራንን የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ችግሮች ምንጭ ለመፈተሽ ጥቅም ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡

በዚህም በቃለ መጠይቅ በተገኘው ውጤት መሰረት ተጠኚ መምህራን በቋንቋ ትምህርት ስልጠና ጊዜ የአንብቦ መረዳት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ስልጠና ቢያገኙም ወደ ስራ አለም ከተቀላቀሉ በኂላ መምህራኑ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነዘዴ ዙሪያ ምንም ዓይነት ስልጠና ወስደው አያውቁም፡፡ ይህም መምህራን በስራ ላይ ለመተግበር እንደሚቸገሩ ያመለክታል፡፡ በቃለ መጠይቁ ላይ የተሳተፉት ሶስት መምህራን በስልጠና ጊዜያገኙትን ትምህርት ተግባር ላይ ለማዋል በአንድ ክፍል ዉስጥ በርካታ ተማሪዎች መኖር እና የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ በቁጥር ዉስን መሆን ዋነኛ ችግሮች መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሁለቱ መምህራን የአየር ንብረቱ ሞቃታማ መሆን እና ለትምህርቱ የተመደበዉ የክፍለ ጊዜ መጠን በሳምንት ሁለት መሆኑ በስልጠና ጊዜ ያገኙትን ትምህርት ተግባር ላይ ለማዋል ችግር እንደፈጠረባቸው አብራርተዋል፡፡ እንዲሁም አንድ መምህር በስልጠና ጊዜ ያገኙትን ትምህርት ተግባር ላይ ለማዋል ከታች ክፍል ይዘዉት የመጡት የንባብ ክሂል ዕዉቀታቸዉ ዝቅተኛ መሆኑ፣ የስምንተኛ ክፍል ማለፊያ ነጥብ ዝቅተኛ መሆኑ እና ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ላይ ለመሳተፍ ፈቃደኛ አለመሆን (ፍላጎት አለመኖር) ሌሎች ተጨማሪ ችግሮች መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

በቃለ መጠይቁ ላይ የተሳተፉት ሶስት መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርት ሲያስተምሩ የአሰሳ ንባብ ንዑስ ክሂልን አዘውትረው እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ እንደአስፈላጊነቱ ሁሉም ተማሪዎች በለሆሳስ ወይም በአርምሞ እንዲያነቡ ሌላ ጊዜ ደግሞ በክፍል ድምፃቸዉን ክፍ አድርገዉ እንዲያነቡ እንደሚያደርጉ አብራርተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሁለቱ መምህራን ከአሰሳ ንባብ በተጨማሪ ተማሪዎች በቤታቸዉ ሰፊ ፅሁፍ እንዲያነቡ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በለሆሳስ ወይም በአርምሞ እንዲያነቡ በደቂቃ ተምኖ መስጠት ሌላዉ ደግሞ በክፍል ድምፃቸዉን ከፍ አድርገዉ እንደሚያስነብቡ አብራርተዋል፡፡

የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ፍላጎት በመምህሩ ጥረትና አቀራረብ ስለመወሰኑ ያላቸውን እምነት እንዲገልጹ ለተጠየቁት ጥያቄም ሁለቱ መምህራን ሙሉ በሙሉ ፍላጎት በመምህሩ ጥረትና አቀራረብ ይወሰናል ብለው መስማማታቸውን ቀሪው አንድ መምህር ደግሞ በከፊል መስማማታቸውን አስረድተዋል፡፡ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ውጤት ከተማሪዎች ፆታ ጋር ያለዉ ዝምድና እንዲገልጹ ሲጠየቁም መምህራን ሁለቱ ሴቶች አንብቦ መረዳት ትምህርትን ለመማር ቢፈልጉም በክፍል ውስጥ እንዲነቡ ሲጠየቁ ፍርሃትና መሸማቀቅ (ሀፍረት) እንደሚስተዋልባቸው አስረድተዋል፡፡ በተመሳሳይ ሶስተኛው መምህር ሴት ተማሪዎች

ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ የማፈርና ተሳትፏቸዉም ዝቅ ያለ ነው በማለት መልሰዋል፡፡ ይህም በአጠቃላይ ሲታይ ሴት ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ትምህርት ውጤታቸው ከወንዶች ዝቅ ሊል እንደሚችል ያመለክታል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# 5. ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳብ

## 5.1. ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ደረጃን መመርመር ነው፡፡ ለዚህም ጥናቱ የሚከተሉትን ሶስት የምርምር መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሮ ነበር፡፡

- በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው?
- የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከተማሪዎች ጾታ ጋር ዝምድና አለውን?
- በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ምን ይመስላል?

የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመመርመርም በመጀመሪያ ተጠኚዎችና መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተመርጠዋል፤ ተዘጋጅተዋል፡፡ በዚህም በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመፈተሽ በ2015 ዓ.ም በትምህርት ቤቱ ተመዝግበው በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

በፓዊ ወረዳ ሰባት መሰናዶና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ ቀጠና ሁለት መንደር ሰባት መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ ቀጠና ሁለት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ቀጠና ሁለት መንደር 49 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ህዳሴ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ቀጠና ሁለት መንደር 14 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ እና ቀጠና ሁለት መንደር 23/45 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች) ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ትምህርት ቤቶች መካከልም አጥኚው የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመፈተሽ ፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት በአመቺ ንሞና ዘዴ በመምረጥ አጥንቷል፡፡

አጥኝው በጥናቱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመፈተሽ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ በመምረጥ ጥናቱን አካሂዷል፡፡ በመሆኑም በትምህርት ቤቱ በ2015 ዓ.ም ተመዝግበው በመማር ላይ ከሚገኙት ሰባት የዘጠነኛ መማሪያ ክፍሎች መካከል ሶስት መማሪያ ክፍሎች የእጣ (ሎተሪ) ንሞና ዘዴን በመጠቀም 9ኛ "B"፣ 9ኛ "C" እና 9ኛ "F" በመምረጥ በመማሪያ ክፍሎቹ ውስጥ የሚገኙ 99 ወንድ እና 95 ሴት በድምሩ 194 ተማሪዎችን በጠቅላይ ንሞና ዘዴ በመምረጥ አጥንቷል፡፡

ጥናቱ በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመፈተሽ የአንብቦ መረዳት ፈተና፣ የክፍል ውስጥ ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳርያነት ተጠቅሟል፡፡

የጥናቱ ንድፍ ከመጠናዊ ምርምር የሚመደብ ሲሆን ገላጭ የምርምር ስልትን ተከትሎ ተካሂዷል፡፡ በጥናቱ ዓላማ መሰረት በቅድሚያ የተፈተሸው የምርምሩ መሰረታዊ ጥያቄ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው? የሚል ነበር፡፡ በዚህም የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታን በሚመለከት የተሰበሰቡ መረጃዎች SPSS 20 ስታቲስቲክስ ሶፍት ዌርን በመጠቀም በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት (One Sample t-test) ፍተሻ ተካሂዷል፡፡ በተገኘው ውጤት መሰረትም በጥናቱ የተሳተፉ 194 ተማሪዎች በመጀመሪያው ፈተና (የሚጠበቅ ውጤት 18.75፣ የተመዘገበ አማካይ ውጤት 14.19)፣ በሁለተኛው ፈተና (የሚጠበቅ ውጤት 18.75፣ የተመዘገበ አማካይ ውጤት 14.71) በአጠቃላይ ፈተና ውጤት ደግሞ (የሚጠበቅ ውጤት 37.50፣ የተመዘገበ አማካይ ውጤት 28.90) ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በተመሳሳይ ተጠኚ ተማሪዎች ባስመዘገቡት አጠቃላይ በአማርኛ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤትና በሚጠበቀው ውጤት መካከል ያለው የልዩነት ጉልህነት ደረጃ $t(193) = 57.777$ $P<0.001$ ሆኖ ስለተገኘ ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) አንሷል፡፡ ይህም የተመዘገበው በአማርኛ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው ውጤት በታች ሆኖ (ዝቅ ብሎ) መገኘት በስታስቲክስ ጉልህ (ተቀባይነት ያለው) መሆኑን ያመለክታል፡፡

በጥናቱ ዓላማ መሰረት በሁለተኛ ደረጃ የተፈተሸው የምርምሩ መሰረታዊ ጥያቄ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከተማሪዎች ጾታ ጋር ዝምድና አለውን? የሚለው ጥያቄ ነበር፡፡ የተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ መረዳት ክሂል ደረጃ ከተማሪዎች ጾታ ጋር ያለውን የተዛምዶ ደረጃ ለመግለጽ የተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ክሂልን በሚመለከት በአንብቦ መረዳት ፈተናዎቹ የተሰበሰቡ መረጃዎች SPSS 20 ስታቲስቲክስ ሶፍት ዌርን በመጠቀም በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Sample t-test) ተሰልተዋል፡፡ በተገኘው ውጤት መሰረትም በጥናቱ የተሳተፉ 99 ወንድ እና 95 ሴት በድምሩ 194 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አማካይ ውጤት በአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ ወንድ ተማሪዎች 14.7677 እና ሴት ተማሪዎች 13.5895፣ በአንብቦ መረዳት ፈተና ሁለት ደግሞ ወንድ ተማሪዎች 15.2929 እና ሴት ተማሪዎች 14.1053 በተመሳሳይ በአጠቃላይ አንብቦ መረዳት ፈተና ወንድ ተማሪዎች 30.0606 እና ሴት ተማሪዎች 27.6947 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በተመሳሳይ የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Sample t-test) ስታትስቲክስ ውጤት ማየት እንደሚቻለው ተጠኚ ተማሪዎች ባስመዘገቡት አጠቃላይ በአማርኛ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤትና በሚጠበቀው ውጤት መካከል ያለው የልዩነት ጉልህነት ደረጃ የወንድ ተማሪዎች $t(98) = 2.393$ $P<0.018$ እንዲሁም የሴት ተማሪዎች $t(94) = 2.405$ $P<0.017$ ሆኖ ስለተገኘ ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) አንሷል፡፡ ይህም በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በወንዶችም በሴቶችም ተማሪዎች የተመዘገበው አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው ውጤት በታች (ዝቅ ብሎ) ሆኖ መገኘትና ከሴቶች ይልቅ ወንዶች የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸው በስታስቲክስ ጉልህ (ተቀባይነት ያለው) መሆኑን ያመለክታል፡፡

በጥናቱ በሶስተኛ ደረጃ የተፈተሸው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የመምህራን የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ምን ይመስላል? የሚል ነበር፡፡ በጥናቱ የመምህራንን የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ለመፈተሽ ጥቅም ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የክፍል ምልከታ ነው፡፡ በዚህም በምልከታ በተገኘው ውጤት መሰረት ተጠኚ መምህራን በቅድመ ንባብ እና በንባብ ጊዜ ተግባራት ላይ ጥቂት ድክመቶች (ወጣገባነት) የተስተዋሉባቸው ቢሆንም እንደአጠቃላይ ሲታይ ጠንካራ (የተሻሉ) መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በተቃራኒው በድህረ ንባብ ትምህርት ተግባራት ደረጃ በጣም ደካማ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህ የመምህራኑ በድህረ ንባብ ትምህርት ተግባራት ደረጃ በጣም ደካማ መሆን ካሉባቸው የቅድመ ንባብና የንባብ ጊዜ ጥቂት ተግባራት ድክመት ጋር ሲደማመር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ይጠቁማል፡፡

## 5.2. መደምደሚያ

ጥናቱ ከላይ የቀረቡትን የጥናቱ ውጤቶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት ድምዳሜዎች ላይ ደርሷል፡፡

- በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የ2015 ዓ.ም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ደረጃ በአማርኛ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው ውጤት በታች (28.90) ነው፡፡ ይህም የተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ደረጃ መካከለኛ (ከ51-60) መሆኑን ያመለክታል፡፡
- በፓዊ ወረዳ የፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂል ደረጃ ከተማሪዎች ጾታ ጋር ዝምድና እንዳለው ሲፈተሽም በአጠቃላይ አንብቦ መረዳት ፈተና ወንድ ተማሪዎች 30.0606 እና ሴት ተማሪዎች 27.6947 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ ከመረዳት አንጻር ከሴቶች ይልቅ ወንዶች የተሻለ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ያመለክታል፡፡
- በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Sample t-test) ስታትስቲክስ ውጤትም ተጠኚ ተማሪዎች ባስመዘገቡት አጠቃላይ በአማርኛ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤትና በሚጠበቀው ውጤት መካከል ያለው የልዩነት ጉልህነት ደረጃ የወንድ ተማሪዎች $t(98) = 2.393$ $P<0.018$ እንዲሁም የሴት ተማሪዎች $t(94) = 2.405$ $P<0.017$ ሆኖ ስለተገኘ ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) አንሷል፡፡ ይህም በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በወንዶችም በሴቶችም ተማሪዎች የተመዘገበው አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው ውጤት በታች (ዝቅ ብሎ) ሆኖ መገኘትና ከሴቶች ይልቅ ወንዶች የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸው በስታስቲክስ ጉልህ (ተቀባይነት ያለው) መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡
- በምልከታ በተገኘው ውጤት መሰረት ተጠኚ መምህራን በቅድመ ንባብ እና በንባብ ጊዜ ተግባራት ላይ ጥቂት ድክመቶች (ወጣገባነት) የተስተዋሉባቸው ቢሆንም እንደአጠቃላይ

ሲታይ ጠንካራ (የተሻሉ) መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በተቃራኒው በድህረ ንባብ ትምህርት ተግባራት ደረጃ በጣም ደካማ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

➢ በቃለ መጠይቅ በተገኘው ውጤት መሰረት ተጠኚ መምህራን በቋንቋ ትምህርት ስልጠና ጊዜ የአንብቦ መረዳት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ስልጠና ቢያገኙም ወደስራ አለም ከተቀላቀሉ በኋላ መምህራኑ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነዘዴ ዙሪያ ምንም ዓይነት ስልጠና ወስደው አያውቁም፡፡ ይህም መምህራን በስራ ላይ ለመተግበር እንደሚቸገሩ ተረጋግጧል፡፡

## 5.3. የመፍትሄ ሃሳብ

የዚህ ጥናት አቅራቢ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ያላቸውን አስተያየቶች በመፍትሄ ሃሳብነት እንደሚከተለው ጠቁሟል፡፡

- መምህራን የተማሪዎቻቸዉን አንብቦ የመረዳት ፍላጎት እንዲያድርባቸዉ በመማሪያ መፅሐፍ ላይ ብቻ ከመመካት ይልቅ የተለያዩ ምንባቦችን በማሰባሰብ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- መምህራን የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ንባብን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ስልጠና ቢሰጣቸው፡፡
- መምህራን የክፍል ዉስጥ የተለያዩ ርዕሶችን በማዘጋጀት በየዕለት ክፍለ ጊዜያቸዉ በንባብ ዙሪያ ዉይይት ቢያዘጋጁ፡፡
- የተማሪ ወላጆችና መምህራን ከሌሎች የትምህርት ባለሙያዎች ጋር በመሆን በሴት ተማሪዎች የንባብ ክሂል ዙሪያ እየተፈጠረባቸዉ ያለዉን ተፅዕኖ ለመቀነስ ቀጣይነት ያለዉ ዉይይት ቢኖር፡፡

## ዋቢዎች


Alderson, C.J. & Urquhart, A.H. (1984). **Reading in Foreign Language.** New York፡ Longman Inc.

Alderson, J.C (2000). **Assessing Reading.** Cambridge: Cambridge University Press.

Gage, N. C. (1963). **Handbook of research on teaching**. Chicago: Rand Mc Nally and Co .

Gariliet, L. (1981). Development of young children's Reading self-concepts: an examination of emerging subcomponents and Their relationship with reading achievement: **Journal of Educational Psychology**. London. Cambridge University Press.

Hager,J,L. (2017). The Relationship of Reading Self Efficacy and Reading Achieve-Ment Seconde Grade Students.Graduate Student Theses, Dissertation,and Professional Papers.11062.

Harmer, J. (1991). **The Practice of English Language Teaching**. New York: Longman.

Heaton,J.B.(1975). **Writing Language Tests**: A Practical Guide for Teachers of English as Second Language Foreign Language. London: Longman.

Hughes,A.(1989). **Testing for Language Teachers.** Cambridge: Cambridge University Press.

Janet Hinchley and Betty Ann Levy. (1988). Developmental and Individual Differences in Reading Comprehension. **Cognition and Instruction.** Cambridge: Cambridge University Press.

Jordan, R. (1993). **Academic Writing Course.** Grafton Street: Hondon.

Kalla, R. (2005). **Reading in the Classroom.** London: Macmillan Publishers,Ltd.

Kroll, Barb.. (1996). **Second Language Writing.** Cambridge. Cambridge University press.

Landah, Knight. (2006) **Learning and Teaching English.** Oxford: Oxford University Press.

Madsen,H.S.(1983). **Techniques in Testing.** New York: Oxford University Press.

May. F.B.(1990). **Reading as Communication in an Interacting Approach** (3rd ed.). New York: Merill Publishing Company.

Narayanaswamy, K.R. ( 1975) "The Measurement of Reading Ability". **ELT Journal** 29 (2) 144-147.

Nelson, H. (1963). "Overcoming Reading Deficiencies at the College Level." **Journal of Developmental Reading**. Vol.6, P.P 238.

Nuttall, G. (1982). **Teaching and Reading Skill Foreign Language**. Chicago, Heineman Educational Book Ltd.

Piculs,W.and L.F.Chard.(2005). **Teaching and Researching Reading.** Hariow: Pearson Education.

Shanahan T. (2006). The National Reading Panel Report: Practical Advice for Teachers. **Learning Point Associates.** Chicago. Chicago University Press.

Ur, P. (1996). **A Course in Language Teaching Practice and Theory**. Great Britain: Cambridge University Press.

Williams,E. (1984). Reading in the Language Classroom. London: London.MacmillanPublishing.

መኮንን ናና፡፡ (2000)፡፡ ***በአዊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ፡፡*** አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ የማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ/ያልታተመ/፡፡

ማስተዋል ዉበቱ፡፡ (1989) የከፍተኙ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ፣ በአዲስ አበባ በሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት፡፡

ማረው ዓለሙ፡፡ (1998)፡፡ **የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ** (የተሻሻለ 2ኛ ዕትም)፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

በየነ ማሞ፡፡ (1986)፡፡ **በአስረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች የብቃት ደረጃ፡፡** አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ የማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ /ያልታተመ/፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡(1996)፡፡ **በስነ-ፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር**፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ተሾመ ፎርሲዶ፡፡ (1997)፡፡ **በደቡብ ኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በከምባታ ጠንባሮ ዞን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ችሎታ፡፡** አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ የማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ /ያልታተመ/፡፡

አለም እሸቱ፡፡ (1995)፡፡ **"በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች አወቃቀር፡፡" ከጥቅምት 25 እስከ 29/1995 ዓ.ም ለአማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጁ የ2ኛ እና የ8ኛ**

**ክፍልች መርሃ ትምህርቶችን ለማሻሻል ለተዘጋጀ አውደ ጥናት የቀረበ** ከስ/ት/ዝ/ጥ/ም ኢንስቲትዩት፣ አዲስ አበባ /ያልታተመ/::

ዘውዱ መብሬ፡፡ (1998)፡፡ **በትግረኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የአማርኛ አሃዶችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ፡፡ የማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፡፡** አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ /ያልታተመ/፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል:: (1999):: **የአማርኛ መዝገበ ቃላት**:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዳዊት ደስታ፡፡ (2008)፡፡ **ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል፡፡** አዲስ አበባ::

ጌትነት ማሞ፡፡ (1990)፡፡ **በጋሞኛ ቋንቋ አፋቸውን በፈቱ የአርባ ምንጭ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መዋቅር እውቀትና በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ጽሁፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ፡፡** የማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ /ያልታተመ/፡፡

**አባሪ "ሀ"**

**<u>የአንብቦ መረዳት ፈተና</u>**

**በፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት**

**የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና (25%)**

**ለፈተና የተሰጠ ሰዓት *<u>1:00</u>*  የተፈታኙ ኮድ ...........**

ይህ ፈተና የእናንተን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት የቀረበ ነው፡፡ ስለሆነም ምንባቡን በጥሞና በማንበብ ለቀረቡ ጥያቄዎች እንደአጠያየቃቸው ተገቢ ምላሽ ስጡ፡፡

**<u>ምንባብ</u>**

ልክ በቀጠሮዉ ሰዓት በመድረሱ ደስ ብሎት ረጅም ቅልጥሙን አመሰገነ፡፡ በስንት ደጅ ጥናት ያገኘዉ ቀጠሮ ነበር፡፡ «ቀጠሮ አለህ?» ብላ ጠየቀችዉ የቢሮዉ ፀሐፊ፡፡ ሽቶዋ ያውዳል፡፡ ጡቶቿ ጠላት ላይ የተደገኑ ሮኬቶች ይመስላሉ፡፡ ጥቁር ሹራብ ለብሳለች፡፡ የልብ ቅርጽ ያለዉ የአንገት ጌጧ ከጡቶቿ መሀል ተሸጉጦ ይታያል፡፡ ቶሎ ብሎ አይኑን ከጡቶቿ ላይ ነቀለ፡፡ ፈገግ አለች ትኩስ የተሸለቀቀ በቆሎ የሚመስሉትን ጥርሶቹን አሳያትና «አዎን ቀጠሮ አለኝ» «ጠብቅ ይመጣሉ» አለችዉ፡፡ የእጅ ቦርሳዋን እየከፈተች፡፡ረጃጅም እጆቿ በጠረንጴዛዉ ሥር ይታያል፡፡ ቀይ ቀለም የተቀቡት አዉራ ጣቶቿ የሚያሾፍበት መሰለዉ፡፡ እንደገና አይን ለአይን ተጋጩ፡፡ ረጃጅም እጆቹን የሚያገባበት ጠፋዉ፡፡ ከት ብላ ሳቀች ምን እንዳሳቃት አልገባዉም፡፡ ጠይም ፊቱ አሻቦ መሰለ፡፡ ወዲያዉኑ ቀጠሮ የሰጠዉ ባለስልጣን መጣ፡፡ ቁመናዉ አጭር ሆኖ ቦርጫም ነበር፡፡«ሌሎች ባለጉዳዮች ሳይመጡ ቶሎ ግባ» አለችዉ ፀሐፊቱ፡፡ የቢሮዉን በር ቀስ ብሎ ከፍቶ ገባ፡፡ ሰዉዬዉ ከትልቁ ጠረንጵዛ ኋላ ትልቅ ወንበር ላይ ተኮፍሷል፡፡ ያ ቅድም ሲገባ ያየዉ አጭር ሰዉ አሁን ግዙፍ መስሎ ታዬዉ፡፡ «ባለፈዉ ሳምንት ለዛሬ ቀጠሮ ሰጥተዉኝ ነበር» አለዉ እጆቹን ወደ ኋላ አድርጎ፡፡ ሳምንቱን ሙሉ ተስፋ የጣለበት ቀጠሮ ነበር፡፡

« እኮ ጉዳይህ ምንድን ነዉ»

«ሥራ ፈልጌ ነበር፡፡»

«ማን ነዉ የላከህ?»

«ማንም እኔዉ ነኝ መጣሁት፡፡»

«የማን ልጅ ነህ?»

የማን ልጅ ነኝ ይበል? መምሬ ሳህሌ፣ አምላካቸዉ ነፍሳቸዉን ይማርውና ማንም አልነበሩም፡፡ ማንም የማያዉቃቸዉ ተራ ቄስ ነበሩ፡፡ ሥራ ሊያስገኝ የሚችል የዘር ሀረግ ከየት አምጥቶ ይምዘዝ! ኢትዮጵያዊነት ብቻዉን አይበቃም፡፡ ሥራ ፈላጊ ሥራ ለማግኘት የአንድ የታወቀ ሰዉ ልጅ ወይም ዘር መሆን ያስፈልገዋል፡ ሥራ ለማግኘት ከወረቀት ድግሪ የተሻለ በመወለድ የሚገኝ የላቀ ድግሪ ኖሯል ለካ! አልታደለም፡፡ ምን ይበል!

«አገርህ የት ነዉ?» «የትዉልድ አካባቢህ ማለቴ ነዉ፡፡ «ለመሆኑ ምሩቅ ነህ?»

«አይደለሁም ሁለት አመት ይቀረናል. . .»

«ትምህርቱን ሳልጨረሰ ቀርቶ ወዳጄ ዛሬ ለምሩቃንም ሥራ ለማግኘት ችግር ነዉ፡፡ ሁሉም የመንግስት ሥራ ፈላጊ ነዉ፡፡ መንግስት ሁሉንም አስተምሮና ሥራ አስይዞ አይችልም፡፡ ለተቀጠሩትም በቂ ሥራ የለም፡፡ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በሥራ ፈቶች ተጣብበዉ ነዉ

የሚታዩት። አዝናለሁ። ምሩቅ ብትሆን እንኳን...» «የለም። ምሩቅ አይደለሁም እርጉም ነኝ... ለእርጉማን አዲስ አበባ ቦታ የላትም፤ መቆሚያ መቀመጫ የላትም፤ ጆሮ የላትም። አዲስ አበባ ልብ የላትም። እንዴት ልብ ይኖራታል? ልቧ በወሲብ፣ በፍቅረ ነዋይና በስልጣን ተገጥቦ አልቋል። ዙፋኑም ጆሮና ልብ የለዉም። ጆሮዉ እንደ እንጦጦ ተራራ ስምንት ሺህ ጫማ ወደላይ ርቋል። በሩን ከፍተዉ ከአዳራሽ ሊገቡ የሚችሉት የዘር ሀረግ እየመዘዙ የእገሌ ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ነኝ በማለት የታደሉት ናቸዉ።

በእድሉ ክፉኛ እያዘነ ከባለስልጣኑ ቢሮ ወጥቶ ሄደ። በድሮ ቄራ መንገድ ሽቅብ ወጥቶ የተረተር ሰፈሩን መንገድ በመያዝ ወደ አራት ኪሎ ሲያመራ አንድ ጥቁር ማርቼዲስ ቤንዚን መኪና በጎማዉ መንገድ ላይ የተኛዉን የዝናብ ዉሃ አልብሶት አለፈ። የባሱኑ ተናደደ። ግን መናደድ የት ሊያደርስ! ንዴቱን ለማብረድ በሀይል ይራመድ ጀመር።

አንድ ወር ሙሉ ሥራ ፍለጋ ሲንከራተት ያልረገጠዉ የመንግስት መስሪያ ቤትና የግል ድርጅት የለም። ያልጠበቀዉ ባልስልጣን፣ ባይኑ ያልገረፈዉ የቢሮ ተላላኪ አልነበረም። ክፍት ቦታ የለንም! ያለሥራ መግባት ክልክል ነዉ! አቤት ተስፋ ሲያስቆርጡ! በጋዜጦች የሚያወጧቸዉም የክፍት ሥራ ቦታ ማስታወቂያዎች ያንኑ ያህል ነበር ተስፋ የሚያስቆርጡት፡ የሁለተኛ አመት የዩንቨርሰቲ ትምህርት ያጠናቀቀ እና የስደስት አመት ሥራ ልምድ ያለዉ ወይም ቢ.ኤ. ድግሪ ኖሮት የሁለት አመት የሥራ ልምድ ያለዉ ወዘተ የሚሉ ናቸዉ። ሥራ ላይ ላሉ ሰዎች እንጂ ገና ሥራ ለሚፈልጉ ሥራ አጦች የታቀዱ ማስታወቂያዎች አይደሉም።

ከጊዜ በኂላ ነበር ማስታወቂያዎቹ ለሚታወቁ ሰዎች እንደ ልብስ በልክ ተሰፍተዉ የሚወጡ መሆናቸዉን የተረዳዉ። በአንድ ወር ዉስጥ ስድስት መስሪያ ቤቶች ባወጧቸዉ የመወዳደሪያ ፈተናዎች ተሳትፏል። አንዱንም አላለፈም። ጎበዝ ተማሪ ከመሆኑም ሌላ ስሙ ከዩንቨርሲቲዉ ዲን የክብር መዝገብ ወጥቶ አያዉቅም። የትምህርት ቤት ጓደኞቹ ባወጡለት ቅጽል ስም «መፀሐፍ ትራሱ» ወይም «ፕሮፌሰር ሀዲስ» እያሉ የሚጠሩት እንዳዉ በዋዛ አልነበረም። ግን ቀላል፣ በጣም ቀላል ነዉ ብሎ ያሰበዉን ፈተና ማለፍ ሲያቅተዉ ምን ይባላል ፈተናዉን ማለፍ ያለበት ሰዉ አስቀድሞ የታወቀ ስለሆነ የሚሰጠዉ ፈተና እንደዉ ለይስሙላ በዉሸት መሆኑ ከገባዉ ሰንበት ብሏል።

(በአሉ ግርማ፣ ሀዲስ። 2005፤ ማንኩሳ አሳታሚ ድርጅት)

***<u>መመሪያ</u> <u>አንድ፤</u>*** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በቀረበው ምንባብ መሰረት ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ ከጥያቄው ፊት ለፊት በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ መልስ ስጥ/ጪ (10%)

1. የቢሮዉ ፀሐፊ ስታናገረዉ «ረጃጅም እጆቹን የሚያገባበት ቦታ ጠፋዉ» የሚለዉ አገላለፅ የትኛዉ ስሜት እንዳለበት ይመለከታል?

   ሀ. ፍቅሩን ለ. ድንጋጤውን ሐ. ፌዘኛነቱን መ. ፍርሀቱን

2. ባለታሪኩ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለመመረቅ ስንት ዓመት ይቀረዋል?

   ሀ. አምስት ለ. ሦስት ሐ. አራት መ. ሁለት

3. «ዙፋኑም ጆሮ ለዉም» ሲል ምን ማለቱ ነዉ?

ሀ. መሪዉ አይሰማም ለ. ጆሮው ተቆርጧል

ሐ. ወንበሩ ጆሮ የለዉም መ. ባለትንሽ ጆሮዉ ነዉ

4. ባለታሪኩ ይብስ የተናደደው ለምንድን ነው?

ሀ. ስራ ስላጣ ለ. ጎርፍ ስለረጨው ሐ. ዘርሀረግ በማጣቱ መ. በሙስና መስፋፋት

5. «አዲስ አበባ ልብ የላትም» ለተባለችበት ምክንያት ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. በወሲብ ልቧ የተገጠበ በመሆኗ ለ. ጆሮ ሰጥታ ማታዳምጥ መሆኗ

ሐ. ፍቅረንዋይ የሚያጠቃት መሆኗ መ. በስልጣን ምትባልግ መሆኗ

6. ማስታወቂያዎቹ እንደ ልብስ በልክ ተሰፍተዉ የሚወጡ ናቸው ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. ታልመው ለ. ተስተካክለው ሐ. ተመጥነው መ. ተብራርተው

7. በጋዜጣ የሚወጡ ማስታወቂያዎች ተስፋ የሚያስቆርጡት ለምንድን ነዉ?

ሀ. ለሥራ አጦች የታቀዱ ማስታወቂያዎች ስለሆኑ

ለ. ለሚታወቁ ሰዎች እንደልብስ በልክ ተሰፍተዉ ስለሚቀርቡ

ሐ. በስራ ላይ ሰዎች ታቅደዉ የማይቀርቡ ስለመሆኑ

መ. አዲስ ምሩቃንን በተገቢዉ መልኩ ስለሚያሳትፉ

8. ባለታሪኩ «መፀሐፍ ትራሱ» የሚል ቅፅል ስም የወጣለት ለምንድን ነዉ?

ሀ. በትራስ ፈንታ መፀሐፍን ስለሚንተራስ ለ. ከጓደኞቹ በትምህርቱ ልቆ በመገኘቱ

ሐ. መፀሐፍ ሻጭ ስለሆነ መ. ትራስ እየሰራ ስለሚሸጥ

9. ስለባለታሪኩ አባት ትክክለኛ ሀሳብ የያዘዉ የቱ ነዉ?

ሀ. አርሶ አደር ለ. ደብተራ ሐ. ቄስ መ. ነጋዴ

10. ከላይ ለቀረበዉ ምንባብ ከሚከተሉት ዉስጥ የተሻለ ርዕስ የሚሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ቀጠሮ አክባሪ ለ. ሥራ ፍለጋ ሐ. ብልሁ ተማሪ መ. የትጋት ሚስጥር

***መመሪያ ሁለት፡-*** ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ለተሰመረባቸዉ ቃላትና ሐረጎች አዉዳዊ **ፍቻቸዉን** የያዘውን ፊደል በመምረጥ ከጥያቄው ፊት ለፊት በተሰጠው ቦታ ጻፍ/ፊ (10%)

11. በስንት ደጅ ጥናት ያገኘዉ ቀጠሮ ነበር፡፡

ሀ. በማጥናት ለ. በመፍራት ሐ. በልመና መ. በመመላለስ

12. ሽቶዋ ያዉዳል፡፡ ሀ. ይሰነፍጣል ለ. ይጣፍጣል ሐ. ይቀረናል መ. ይጣራል

13. ቶሎ ብሎ ከጡቶቿ ላይ አይኑን ነቀለ፡፡
ሀ. አይኑን አወጣ ለ. አፍጥጦ ቀረ ሐ. እይታውን ቀየረ መ. አይኑ ፈዞ ቀረ

14. ሰዉዬዉ ቀደም ብሎ ከትልቁ ጠረንጴዛ ኋላ ትልቅ ወንበር ላይ ተኮስፍሏል፡፡
ሀ. ተቀምጧል ለ. ተኝቷል ሐ. ኮርቷል መ. ተንጠራርቷል

15. ፊቱ አሻቦ መስሏል፡፡
ሀ. ለስልሷል ለ. ገርጥቷል ሐ. ወርጭቷል መ. አምሯል

16. የዘር ሀረግ እየመዘዙ .... ለሚለዉ ሀረግ ማሙያ ሊሆን የሚችለዉ የቱ ነዉ?
ሀ. እየቆረጡ ለ. እየሳቡ ሐ. እየቆጠሩ መ. እየሸፈቱ

17. ባይኑ ያልገረፈዉ የቢሮ ተላላኪ አልነበረም፡፡
ሀ. የሰደበዉ ለ. የገረፈዉ ሐ. የገላመጠዉ መ.
ያጠቀሰዉ

18. ጡቶቿ ጠላት ላይ የተደገኑ ሮኬቶች ይመስላሉ፡፡
ሀ.የተቀመጡ ለ.ያነጣጠሩ ሐ.የሰፈሩ መ.የወደቁ

19. የሚሰጠዉ ፈተና እንደዉ ለይስሙላ መሆኑ ከገባዉ ሰንበት ብሏል፡፡
ሀ. ለመፈተሽ ለ. ለማረጋገጥ ሐ. ለማስመሰል መ. ለማሰማት

20. ምሩቅ አይደለሁም እርጉም ነኝ፡፡ ሀ. ክፉ ለ. እድለቢስ ሐ. የተጠላ መ.
የተመሰገነ

***መመሪያ ሶስት፤*** ቀጥሎ በ"**ሀ**" እና በ"**ለ**" ምድብ ቃላትና ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም በምንባቡ መሰረት በ"**ሀ**" ምድብ ለቀረቡ ሃሳቦች በ"**ለ**" ምድብ ከተዘረዘሩት መካከል የሚመሳሰላቸውን ሃሳብ በመምረጥ ከፊት ለፊት በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ መልስ ስጥ/ጪ፡፡ (5%)

| **"ሀ"** | **"ለ"** |
|---|---|
| .......... 21. የአንገት ጌጥ ቅርጽ | ሀ. ሰማያዊ |
| .......... 22. የሹራቧ ቀለም | ለ. ጥቁር |
| ...........23. የጥርሱ ንጽህና | መ.አረንጓዴ |
| .......... 24. የመኪና ቀለም | ሠ. ቢጫ |
| .......... 25. የጥፍሯ ቀለም | ረ. ነጭ |
| | ሸ. ልብ ቅርጽ |
| | ቀ. ወይንጠጅ |
| | በ. ቀይ |
| | ተ. አሳ ቅርጽ |
| | ቸ. ሮዝ |

## አባሪ “ለ”
## የአንብቦ መረዳት ፈተና
### በፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና (25%)

**ለፈተና የተሰጠ ሰዓት 1:30** **የተፈታኙ ኮድ ..........**

ይህ ፈተና የእናንተን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት የቀረበ ነው፡፡ ስለሆነም ምንባቡን በጥሞና በማንበብ ለቀረቡ ጥያቄዎች እንደአጠያየቃቸው ተገቢ ምላሽ ስጡ፡፡

### የኖቤል ተሸላሚዋ ኢትዮጵያዊት

አካል ጉዳተኝነት በብዙዎች ዘንድ እንደ እርግማንና እንደ መጥፎ ነገር በሚታይበት በዚህም የተነሳ አካል ጉዳተኞች የመገለል እጣ በሚደርስባቸው ሀገራችን ገጠራማ አካባቢ ነው የተወለደችው፡፡ የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማቋቋሚያ ማዕከል በተባለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ውስጥ በሥራ አስኪያጅነት በማገልገል ላይ ትገኛለች፡፡ አካል ጉዳተኝነት ከስኬት እንደማያስቀር በተግባር ማሳያ መሆኗን መልዓክ ሹክ ሳይላቸው አልቀረምና ወላጆቿ ስሟን ሲያወጡ የትነበርሽ አሏት፡፡ የትነበርሽ ንጉሴ ጥር 24 ቀን በ1975 ወሎ አማራ ሳይንት ነው የተወለደችው፡፡

የትነበርሽ በስድስት ዓመቷ ባጋጠማት የማጅራት ገትር ሕመም የተነሳ የዓይን ብርሃኗን በማጣቷ ከአያቶቿ ጋር ለመኖር ወደ አዲስ አበባ መጣች፡፡ ሆኖም አዲስ አበባ ለዓይነ ስውራን የሚሆን ትምህርት ቤት ባለመኖሩ ወደ ሻሸመኔ ተልካ እስከ ስድስተኛ ክፍል ተምራ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰች፡፡ ከሰባተኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል የተማረችበት ዳግማዊ ምንሊክ ትምህርት ቤት ለእሷ አዲስ ሕይወት እንደመጀመር ነበር፡፡ ምክንያቱም ከ16 - 20 ተማሪዎች ብቻ ባሉበት ክፍል ትማር የነበረች ልጅ በአንድ ጊዜ ከሰባ ልጆች ጋር ስትቀላቀል ገሃነም የጣሏት ያህል ተሰምቷታል፡፡ አይነስውር በመሆኗም እሷን ለማቅረብ ፈቃደኞች አልነበሩም፡፡ ተማሪዎች ቢያገሏትም አልቅሳና ተለማምጣ እንዲቀርቧት ከማድረግ ይልቅ በትምህርቷም ሆነ ባሏት የተለያዩ ችሎታዎች ተጠቅማ ያራቃትን ማህበረሰብ በማቅረብ ድንቅ ብቃቷን በተግባር አስመሰከረች፡፡

የሕግ ባለሙያዋ ወ/ሮ የትነበርሽ ለተለያዩ ችግሮች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መፍትሔዎችን በማፈላለግ የተሻለች ዓለም ለመፍጠር ለሰሩ ትጉህ ግለሰቦችና ድርጅቶች የሚሰጠው ራይት ላይቭሊሁድ የተባለው አማራጭ የኖቤል ሽልማትን አግኝታለች፡፡ ድርጅቱ እንዳስታወቀው፣ የ35 ዓመቷ ወ/ሮ የትነበርሽ ለሽልማት የበቃችው የአካል ጉዳተኞችን ሁኔታ ለማሻሻል፣ የሴቶችና ልጃገረዶችን መብት ለማስከበር፣ አካል ጉዳተኞች በትምህርቱና ሌሎች ዘርፎች የማያገል አካታች ሥርዓት ለመፍጠር ባደረገችው ያልተቆጠበ ጥረቷ ነው፡፡

ወ/ሮ የትነበርሽ ለአካል ጉዳተኞች እኩልነት መታገል ከጀመረች ብዙ ዓመታት ሆኗታል፡፡ የትነበርሽ ለአካል ጉዳተኞች መብት መሟገት የጀመረችው በዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርቷን በመከታተል ላይ በነበረችበት ወቅት ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ውስጥ እርሷን ጨምሮ፣ ለአይነ ስውራን ተማሪዎች የብሬይል መጽሐፍ እንዲዘጋጅ አስተዋፅዖ አድርጋለች፡፡ በአሁኑ

ሰዓትም በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ የአካል ጉዳተኞች መብት፣ የግንዛቤ ማስጨበጫና ሰብዓዊ መብቶችና ዕድሎች ለመሟገት የሕግ ሙያ ስራዋን በመተው ሙሉ ጊዜዋን ሰጥታ እየሰራች ትገኛለች፡፡ ለዚህም ዋነኛው ምክንያቷ በማይመች ሁኔታ፣ መሰረታዊ መብቶቻቸው የተነፈጋቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ አካል ጉዳተኞች መኖራቸውን እንዲሁም ችሎታ፣ አቅምና ብቃት እያላቸው ዕድል መነፈጋቸው መሆኑን ትናገራለች፡፡ ለዓይነ ስውራን በተከፈተ የመጀመሪያ ደረጃ አዳሪ ትምህርት ቤት ገብታ ትምህርቷን የመከታተል እድል ማግኘቷ የዕድሏን በር እንደከፈተላትና አካል ጉዳተኝነት ሊያስከትላቸው ከሚችሉ ችግሮች ነፃ እንዳወጣት ዛሬ የምትናገረው ወ/ሮ የትነበርሽ በተለይ አካል ጉዳተኞች የሚያጋጥማቸውን ችግር ሊያሸንፉ የሚችሉት በትምህርት ነው ብላ ስለምታምን ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ ትሰራለች፡፡

የሕግ ባለሙያና የመብት ተሟጋች ወ/ሮ የትነበርሽ የአማራጭ ኖቤል ተሸላሚ ሆኖ መመረጥ ያስገኘላት ዓለም አቀፍ እውቅና ከፍተኛ ኃላፊነት በመያዙ ኃላፊነቷን ለመወጣት ይረዳት ዘንድ የማይፈራ ትውልድ ለማፍራትና በተለይ በሴት አካል ጉዳተኞችና ሴት ሕፃናት ትምህርት ላይ በይበልጥ አተኩራ የመስራት እቅድ እንዳላት ተናግራለች፡፡

ወ/ሮ የትነበርሽ 315,000 ዩሮ የያዘውን አማራጭ የኖቤል ሽልማት ከህንዳዊ ጠበቃ ኮሊን ጎንሳልቬስ እና ከአዘርባጃኗ ጋዜጠኛ ኻድጃ ኢስማይሎቫ ጋር ተጋርታለች፡፡ አሜሪካዊው ጠበቃ ሮበርት ቢለት ደግሞ የክብር ተሸላሚ ሆነዋል፡፡ ራይት ላይቭሊ ሁድ የሽልማት ፋውንዴሽን ለተለያዩ የዓለማችን ችግሮች ተግባራዊ መፍትሄዎችን ለማምጣት ለሠሩ ታታሪ ግለሰቦችና ድርጅቶች ዕውቅና የሚሰጥ፣ ለሰዎች ህይወት መሻሻል አወንታዊ አስተዋፅዖ ያበረከቱ ግለሰቦችን በማበረታታት ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ዓለምቀፍ ድርጅት ነው፡፡

(***ምንጭ***:- አዲስ አድማስ ጋዜጣ፣ የካቲት 10/2008 ዓ.ም ተሻሽሎ የተወሰደ)

***<u>ትዕዛዝ አንድ፤</u>*** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በቀረበው ምንባብ መሰረት ሀሳቡ ትክክል ከሆነ "**እውነት**" ትክክል ካልሆነ "**ሀሰት**" በማለት ከጥያቄው ፊትለፊት በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ መልስ ስጥ/ጪ. (10%)

........... 1. የትነበርሽ የዓይን ብርሃኗን ያጣችው ስድስት ዓመት ከሞላት በኋላ ነው፡፡

........... 2. የትነበርሽ በአንድ ጊዜ ከሰባ ልጆች ጋር ስትቀላቀል ገሃነም የጣሏት ያህል ተሰምቷታል፡፡

........... 3. አካል ጉዳተኞች የመገለል እጣ የሚደርስባቸው በብዙዎች ዘንድ እንደ እርግማንና እንደ መጥፎ ነገር ስለሚታይ ነው፡፡

........... 4. አካል ጉዳተኝነት ሊያስከትላቸው ከሚችሉ ችግሮች ነፃ ያወጣት ለዓይነ ስውራን በተከፈተ የመጀመሪያ ደረጃ አዳሪ ትምህርት ቤት ገብታ ትምህርቷን መከታተሏ ነው፡፡

........... 5. የትነበርሽ ለሽልማት የበቃችው የአካል ጉዳተኞችን ሁኔታ ለማሻሻል፣ የሴቶችና ልጃገረዶችን መብት ለማስከበር፣ አካል ጉዳተኞች በትምህርቱና ሌሎች ዘርፎች የማያገል አካታች ሥርዓት ለመፍጠር ባደረገችው ያልተቆጠበ ጥረቷ ነው፡፡

...........6. ወላጆቿ ስሟን ሲያወጡ የትነበርሽ ያሏት አካል ጉዳተኝነት ከስኬት እንደማያስቀራት ስለሚያውቁ ነው፡፡

...........7. የትነበርሽ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን የተማረችው አዲስ አበባ ውስጥ ነበር፡፡

...........8. የትነበርሽ ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ የምትሰራው አካል ጉዳተኞች የሚያጋጥማቸውን ችግር ሊያሸንፉ የሚችሉት በትምህርት ነው ብላ ስለምታምን ነው፡፡

...........9. ባለታሪኳ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ሲያገሏት አልቅሳና ተለማምጣ እንዲቀርቧት የማድረግ ብቃት ነበራት፡፡

...........10. የትነበርሽ ለአካል ጉዳተኞች መብት መሟገት የጀመረችው የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማቋቋሚያ ማዕከል እንደተቀጠረች ነው፡፡

**ትዕዛዝ ሁለት፤** ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ከጥያቄው ፊት ለፊት በተሰጠው ቦታ ጻፍ/ፊ፡፡ (10%)

...........11. ከየትነበርሽ ጋር 315,000 ዩሮ ያልተካፈለው ማን ነው?

ሀ. ኮሊን ጎንሳልቬስ ለ. ኻድጃ ኢስማይሎቫ ሐ. ሮበርት ቢለት መ. ሁሉም

.........12. የትነበርሽ ከሰባተኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል የተማረችው ........... ትምህርት ቤት ነው፡፡

ሀ. የአይነስውራን አዳሪ ለ. ዳግማዊ ምንሊክ

ሐ. ሻሸመኔ ሁለተኛ ደረጃ መ. ሞዴል ሁለተኛ ደረጃ

...........13. የትነበርሽ የማትሰራው ስራ የቱ ነው?

ሀ. ለአካል ጉዳተኞች መብት መሟገት

ለ. ስለአካል ጉዳተኞች መብት ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት

ሐ. ለአካል ጉዳተኞች ሰብዓዊ መብቶች መከበር መታገል

መ. አካል ጉዳተኞችን በዝቅተኛ ዋጋ ማገልገል

........... 14. አካል ጉዳተኞች የተነፈጋቸው ነገር ምንድን ነው?

ሀ. ችሎታ ለ. አቅም ሐ. ብቃት መ. እድል

........... 15. የትነበርሽ የአማራጭ ኖቤል ተሸላሚ ሆኖ መመረጥ ያስገኘላት ነገር ቢኖር ......... ነው፡፡

ሀ. ድርብ ኃላፊነት ለ. የገንዘብ ተካፋይነት ሐ. ዓለም አቀፍ እውቅና መ. ሁሉም

........... 16. የትነበርሽን ለአይነ ስውርነት ያበቃት ምንድን ነው?

ሀ. ትራኮማ ለ. ማጅራትገትር ሐ. መኪናአደጋ መ. መልሱ የለም

.......... 17. ራይት ላይቭሊ ሁድ የሽልማት ፋውንዴሽን እውቅና የሚሰጠው .............ነው፡፡

ሀ. ለሰዎች ህይወት መሻሻል አወንታዊ አስተዋፅዖ ላበረከቱ ግለሰቦች

ለ. ተግባራዊ መፍትሄዎችን ለማምጣት ለሠሩ ታታሪ ግለሰቦች

ሐ. ተግባራዊ መፍትሄዎችን ለማምጣት ለሠሩ ድርጂቶች

መ. ሁሉም

.......... 18. የትነበርሽ በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ ያደረገችው አስተዋጾ ......... ነው፡፡

ሀ. የብሬይል መጽሕፍት እንዲዘጋጅ ማድረግ ለ. ለሰብዓዊ መብቶች መሟገት ሐ. አካታች ሥርዓት መፍጠር

መ. ሁሉም

.......... 19. የትነበርሽ የሕግ ሙያ ስራዋን በመተው የሙሉ ጊዜዋን ሰጥታ እንድትሰራ ያደረጋት አካል ጉዳተኞች.... ነው፡፡

ሀ. በማይመች ሁኔታ መገኘታቸው ለ. መሰረታዊ መብቶቻቸው መነፈጉ

ሐ. ዕድል መነፈጋቸው መ. ሁሉም

.......... 20. የትነበርሽ የተወለደችበት ቦታ ........... ነው፡፡

ሀ. ሳይንት ለ. ሻሸመኔ ሐ. አዲስ አበባ መ. ጋይንት

**<u>ትዕዛዝ ሶስት፤</u>** ቀጥሎ በ"**ሀ**" እና በ"**ለ**" ምድብ ቃላትና ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም በምንባቡ መሰረት በ"**ሀ**" ምድብ ለቀረቡ ሃሳቦች በ"**ለ**" ምድብ ከተዘረዘሩት መካከል በፍቺ የሚመሳሰላቸውን ሃሳብ በመምረጥ ከፊት ለፊት በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ መልስ ስጥ/ጪ፡፡ (5%)

**<u>"ሀ"</u>**

.......... 21. ማግለል

.......... 22. ማካተት

...........23. ማፍራት

.......... 24. ማበረታታት

.......... 25. ማቅረብ

**<u>"ለ"</u>**

ሀ. ማጠናከር

ለ. መታጠፍ

መ. መቋጠር

ሠ. መቀራመት

ረ. መጨመር

ሸ. መነጠል

ቀ. መፍጠር

በ. ጎራ ማለት

ተ. ማፍረስ

ቸ. መርታት

አ. ማሸት

## አባሪ "ሐ"

### የክፍል ዉስጥ ምልከታ

የአንብቦ መረዳት ትምህርት ሲሰጥ መምህሩ የሚያከናዉናቸዉ የተለያዩ ተግባራት ለመከታተል የተዘጋጁ የምልከታ መከታተያ ቅፅ

የመምህሩ መለያ ኮድ (ስም):-……………………………………….

ክፍለ ጊዜ፡-አንድ

የትምህርት ቤት ስም፡- ፓዊ መሰናዶ

ርዕስ፡- "ለወሬ ሞትኩ ይበሉ"

***መመሪያ:-*** በዝርዝር የቀረቡትን ሀሳቦች ተከናወኑዉ ከሆነ ይህን (✓) በመጠቀም አመልክት/ች

| ተ.ቁ | የክፍል ዉስጥ አቀራረብ ይዘቶች | ተከናዉነዋል | አልተከናወነም | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| | **1.ቅድመ ንባብ** | | | |
| 1.1 | ተማሪዎች የሚነቡበትን ምክንያት እስተዋዉቀዋል፣ | | | |
| 1.2 | ተማሪዎች የአንባቦ መረዳት ፍላጎት እንዲያድርባቸዉ አድርገዋል፣ | | | |
| 1.3 | ተማሪዎች የቀደመ ዕዉቀታቸዉን አሁን ከሚማሩት ንባብ ጋር እንዲያያዩዘት አነቃቅተዋል | | | |
| 1.4 | የዕለቱን የአንብቦ መረዳት ትምህርት ርዕስ አስተዋዉቀዋል | | | |
| 1.5 | በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል አድርገዋል፣ | | | |
| 1.6 | ተማሪዎች እንዲወያዩ አድረገዋል፣ | | | |
| 1.7 | ለቁልፍ ቃላት ፍቺ ሰጥተዋል፣ | | | |
| | **2.ጊዜ ንባብ ተግባራት** | | | |
| 2.1 | ጥያቄዎችን በመስጠት አንብቦ መረዳት ክሂል እንዲከናወን አድርገዋል፣ | | | |
| 2.2 | ለንባቡ ጊዜ ወስነዉ (ደቂቃ) ሰጥተዋል፣ | | | |
| 2.3 | ለተጠየቁት ጥያቄ ሞጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል፣ | | | |
| 2.4 | ስዕልን ወይም ምስልን ማንበብ ወይም ቅፅ መሙላት መልመጃዎችን እንዲሰሩ አድረገዋል፣ | | | |
| 2.5 | ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ አድርገዋል፣ | | | |
| 2.6 | የቃላት ፍቺ ከአዉድ አንፃር እንዲገምቱ አድርገዋል፣ | | | |
| | **3.ድህረ ንባብ ተግባራት** | | | |
| 3.1 | ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳታቸዉን መምህሩ ጥያቄ በመጠየቅ አረጋግጠዋል፣ | | | |
| 3.2 | ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸዉ ገጠመኝ ጋር እንዲያይዙት አድርገዋል፣ | | | |
| 3.3 | ተማሪዎች ምንባብ እንዲገመግሙ አድርገዋል፣ | | | |
| 3.4 | ከንባቡ ጋር ሌሎች ክሂሎች ጋር በማጣመር ጥያቄ አቅርበዋል፣ | | | |

አባሪ "መ"

# የክፍል ዉስጥ ምልከታ

የአንብቦ መረዳት ትምህርት ሲሰጥ መምህሩ የሚያከናዉናቸዉ የተለያዩ ተግባራት ለመከታተል የተዘጋጁ የምልከታ መከታተያ ቅፅ

የመመረህሩ መለያ ኮድ (ስም)፡- ………………..

ክፍለ ጊዜ፡-ሁለት

ቀን፡-15/06/2015 ዓ.ም

የትምህርት ቤት ስም፡- ፓዊ መሰናዶ ት/ቤት

ርዕስ፡-ምዕራፍ 6፡- ስደተኛዉ አባይና ሙዚቃ (የግጥም ምንባብ)

**መመሪያ፡-** በዝርዝር የቀረቡትን ሀሳቦች ተከናወኑዉ ከሆነ ይህን (✓) በመጠቀም አመልክት/ች

| ተ.ቁ | የክፍል ዉስጥ አቀራረብ ይዘቶች | ተከናዉነዋል | አልተከናወነም | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| | **1.ቅድመ ንባብ** | | | |
| 1.1 | ተማሪዎች የሚነቡበትን ምክንያት እሰተዋዉቀዋል፣ | | | |
| 1.2 | ተማሪዎችየአንባቦ መረዳት ፍላጎት እንዲያድርባቸዉ አድርገዋል፣ | | | |
| 1.3 | ተማሪዎች የቀደመ ዕዉቀታቸዉን አሁን ከሚማሩት ንባብ ጋር እንዲያያዩዘት አነቃቅተዋል | | | |
| 1.4 | የዕለቱን የአንብቦ መረዳት ትምህርት ርዕስ አስተዋዉቀዋል | | | |
| 1.5 | በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል አድርገዋል፣ | | | |
| 1.6 | ተማሪዎች እንዲወያዩ አድረገዋል፣ | | | |
| 1.7 | ለቁልፍ ቃላት ፍቺ ሰጥተዋል፣ | | | |
| | **2.ጊዜ ንባብ ተግባራት** | | | |
| 2.1 | ጥያቄዎችን በመስጠት አንብቦ መረዳት ክሂል እንዲከናወን አድርገዋል፣ | | | |
| 2.2 | ለንባቡ ጊዜ ወስነዉ (ደቂቃ) ሰጥተዋል፣ | | | |
| 2.3 | ለተጠየቁት ጥያቄ ሞጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል፣ | | | |
| 2.4 | ስዕልን ወይም ምስልን ማንበብ ወይም ቅፅ መሙላት መልመጃዎችን እንዲሰሩ አድረገዋል፣ | | | |
| 2.5 | ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ አድርገዋል፣ | | | |
| 2.6 | የቃላት ፍቺ ከአዉድ አንፃር እንዲገምቱ አድርገዋል፣ | | | |
| | **3.ድህረ ንባብ ተግባራት** | | | |
| 3.1 | ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳታቸዉን መምህሩ ጥያቄ በመጠየቅ አረጋግጠዋል፣ | | | |
| 3.2 | ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸዉ ገጠመኝ ጋር እንዲያይዙት አድርገዋል፣ | | | |
| 3.3 | ተማሪዎች ምንባብ እንዲገመግሙ አድርገዋል፣ | | | |
| 3.4 | ከንባቡ ጋር ሌሎች ክሂሎች ጋር በማጣመር ጥያቄ አቅርበዋል፣ | | | |

## አባሪ "ሠ"

## የክፍል ዉስጥ ምልከታ

የአንብቦ መረዳት ትምህርት ሲሰጥ መምህሩ የሚያከናዉናቸዉ የተለያዩ ተግባራት ለመከታተል የተዘጋጁ የምልከታ መከታተያ ቅፅ

የመመረህሩ መለያ ኮድ (ስም)፡- ……………………

ክፍለ ጊዜ፡- ሶሰት

ቀን፡-04/07/2015 ዓ.ም

የትምህርት ቤት ስም፡- ፓዊ መሰናዶ ት/ቤት

ርዕስ፡- ምዕራፍ 7 አካባቢያችን ቆሻሻና አወጋገዱ

**መመሪያ፡-** በዝርዝር የቀረቡትን ሀሳቦች ተከናወኑዉ ከሆነ ይህን (✓) በመጠቀም አመልክት/ቺ

| ተ.ቁ | የክፍል ዉስጥ አቀራረብ ይዘቶች | ተከናዉነዋል | አልተከናወነም | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| | **1.ቅድመ ንባብ** | | | |
| 1.1 | ተማሪዎች የሚነቡበትን ምክንያት እሰተዋዉቀዋል፣ | | | |
| 1.2 | ተማሪዎች የአንባቦ መረዳት ፍላጎት እንዲያድርባቸዉአድርገዋል፣ | | | |
| 1.3 | ተማሪዎች የቀደመ ዕዉቀታቸዉን አሁን ከሚማሩት ንባብ ጋር እንዲያያዩዘት አነቃቅተዋል | | | |
| 1.4 | የዕለቱን የአንብቦ መረዳት ትምህርት ርዕስ አስተዋዉቀዋል | | | |
| 1.5 | በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል አድርገዋል፣ | | | |
| 1.6 | ተማሪዎች እንዲወያዩ አድረገዋል፣ | | | |
| 1.7 | ለቁልፍ ቃላት ፍቺ ሰጥተዋል፣ | | | |
| | **2.ጊዜ ንባብ ተግባራት** | | | |
| 2.1 | ጥያቄዎችን በመስጠት አንብቦ መረዳት ክሂል እንዲከናወን አድርገዋል፣ | | | |
| 2.2 | ለንባቡ ጊዜ ወስነዉ (ደቂቃ) ሰጥተዋል፣ | | | |
| 2.3 | ለተጠየቁት ጥያቄ ሞጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል፣ | | | |
| 2.4 | ስዕልን ወይም ምስልን ማንበብ ወይም ቅፅ መሙላት መልመጃዎችን እንዲሰሩ አድረገዋል፣ | | | |
| 2.5 | ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ አድርገዋል፣ | | | |
| 2.6 | የቃላት ፍቺ ከአዉድ አንፃር እንዲገምቱ አድርገዋል፣ | | | |
| | **3.ድህረ ንባብ ተግባራት** | | | |
| 3.1 | ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳታቸዉን መምህሩ ጥያቄ በመጠየቅ አረጋግጠዋል፣ | | | |
| 3.2 | ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸዉ ገጠመኝ ጋር እንዲያይዙት አድርገዋል፣ | | | |
| 3.3 | ተማሪዎች ምንባብ እንዲገመግሙ አድርገዋል፣ | | | |
| 3.4 | ከንባቡ ጋር ሌሎች ክሂሎች ጋር በማጣመር ጥያቄ አቅርበዋል፣ | | | |

## አባሪ "ረ"

**ለመምህራን የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ**

የአንብቦ መረዳት ትምህርት ሲሰጥ መምህሩ የሚያከናዉናቸዉ የተለያዩ ተግባራት ለመከታተል የተዘጋጁ ቃለ መጠይቅ

የመምህሩ መለያ ኮድ ____________

የት/ቤቱ ስም፡- ፓዊ መሰናዶ ት/ቤት

በፓዊ መሰናዶ ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ

1. በትምህርት ስልጠና ጊዜ የአንብቦ መረዳት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ በበቂ ሁኔታ ስልጠና አግኝቻለሁ ብለዉ ያምናሉ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________፡፡

2. በስልጠና ጊዜ ያገኙትን ተግባር ላይ ለማዋል ችለዋል? ካልቻሉስ ችግሩ ምንድነዉ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________፡፡

3. የአንብቦ መረዳት ትምህርት ሲያስተምሩ አዘዉትረዉ የሚጠቀሙት የትኞቹን የንዑሳን የንባብ ክሂሎችን ነዉ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________፡፡

4. የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ፍላጎት በመምህሩ ጥረትና አቀራረብ ይወሰናል ብለዉ ያምናሉ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________፡፡

5. የአንብቦ መረዳት ትምህርት ከተማሪዎች ዖታ ጋር ያለዉ ዝምድና ምን ይመስላል?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________፡፡

ስለ ትብብርዎ አመሰግናለሁ፡፡

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለፀዉና የፈረምኩት ይህ ጥናት የራሴ ስራ መሆኑን በጥናቱ ዉስጥ የተጠቀምኩባቸዉም ተዛማጁ ፅሁፎችና መረጃዎች በትክክል በመጥቀስ የተጠቀምኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ፡- ወርቅነህ ይርጋ ደምሴ

ፊርማ፡-……………………….

አድራሻ ፡- **አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሁፍ ፎክሎር ትምህርት ክፍል**